የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን

# የ2018 በጀት ዓመት የዕቅድ ክንውን አመታዊ ሪፖርት

ሰኔ /2018

ኢ.ግ.ባ

አዲስ አበባ

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

1. መግቢያ 2

1. ውጤታማነቱ፣ ጥራቱና ተስማሚነቱ የተረጋገጠ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ ኢንስፔክሽን ማካሄድ 3

**2. የዕጽዋት ምርትና ግብዓት ጥራት ቁጥጥር ዘርፍ........................................................4**

2.1 የፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ 4

2.2 ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች 8

ጤንነቱ፣ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች 8

**2.3 በላቦራቶሪ የጥራት ፍተሻ የተደረገላቸው የ ዕጽዋት ዘር፣ ምርትና የ ዕጽዋት ውጤቶች** 15

**2.4 የዕጽዋት ዘርና ዝርያ ቁጥጥር** 16

**3 የእንሰሳት ግብዓቶች ምርቶች እና አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር** 18

**3.1 የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ** 18

3.2 በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች 24

3.3 የእንስሳት መድኃኒት ጥራት፣ ደህንነትና ፈዋሽነትን ማረጋገጥ 25

3.4 ጥራትና ደህነነቱ የተረጋገጠ የእንሰሳት መኖ 29

3.5 ደረጃውን የጠበቀ የእንሰሳት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት የእንስሳት ውጤቶች ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ 33

4. ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች 41

የበጀት አጠቃቀም 59

**5. በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች፣ የተወሰዱ እርምጃዎች እና በቀጣይ ሊወሰዱ የሚገቡ መፍትሄዎች** 60

6.የተሰጡ መፍትሄዎች 60

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የግብርናው ሴክተር የ10 ዓመትና የመካከለኛ ዘመን ስትራቴጂክ ዕቅድ አካል የሆነውን የግብርና ሬጉላቶሪ ዕቅድ መሠረት በማድረግ፣ የ2018 በጀት ዓመትን በላቀ ክንውንና ስኬት አጠናቋል። ባለፉት 12 ወራት ከተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት መካከል፤ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ባለድርሻ አካላት ጋር የተመሰረቱ ስልታዊ ቅንጅቶች፣ የትብብርና የውል ስምምነት ፕሮቶኮሎች፣ ለክልል አስፈጻሚ አካላት የተደረጉ የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች፣ እንዲሁም የተካሄዱ የዳሰሳ ጥናቶች ተጠቃሽ ናቸው።

በተጨማሪም፣ የቁጥጥር ሥርዓቱን ይበልጥ ቀልጣፋ ለማድረግ የተጀመሩ የዲጂታላይዜሽን ስራዎችና የሕግ ማዕቀፍ ማሻሻያዎች በልዩ ትኩረት የተከናወኑ ሲሆን፤ ተቋሙ ያለውን የሰው ኃይልና ምድብ ሀብት በአግባቡ በመጠቀም ያስመዘገባቸው አበይት ውጤቶች በዚህ ሪፖርት ተካተዋል።

## የኢትዮጵያ ግብርና ባልስልጣን የ2018 በጀት አመት የ12 ወራት ክንውን የግብርና ቁጥጥር ስራዎች

1. ውጤታማነቱ፣ ጥራቱና ተስማሚነቱ የተረጋገጠ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ ኢንስፔክሽን ማካሄድ

- በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ለ 34 የምርምር፣ የኤክስቴሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ብቃታ በኢንስፔክሽን ለማረጋገጥ ታቅዶ ለ39 ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ሆኗል፡፡ይህም በረቂቅ መመሪያዎች የተዘረዘሩ መስፈርቶችን መነሻ በማድረግ 16 የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ስጪ ድርጅት፣ 1 የግብርና መሳሪያ ገጣጣሚ ድርጅት እና 1 የግብርና መሳሪያ አስመጪ ድርጅት፤ 16 የግብርና ምርምር ዘርፎች በድምሩ 18 ተቋማት በሙከራ ኢንስፔክሽን ብቁ መሆናችውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት

- በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ለ 10 የግብርና ምርምር፣ የኤክስቴሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ አልተከናወንም፤ይህም የሆነበት እየተዘጋጁ ያሉ የኤክስቴንሽን አዋጅ፣ የምርምር ቁጥጥር መመሪያ፣ የመካናይዜሽን ቁጥር መመሪያዎች በዝግጅት ሂደት ላይ በመሆናቸው ነው፡፡

### የዳሰሳ ጥናት

- በዓመቱ በግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ሬጉላቶሪ ስራዎችን ለማሳለጥ ሦስት የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ ሦስቱም ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙም 100% ሆኗል፡፡ ይህም የግብርና መሳሪያ ጥራትን በተመለከተ በ12 የግብርና መሳሪያ አምራች እና አስመጪ ተቋማት እንዲሁም የግብርና ምርምር አሰራርን በተመለከተ በ6 የግብርና ምርምር ተቋማት ላይ የዳሰሳ ጥናቱ ተከናውኗል፡፡

### የህግ ማዕቀፍ/ሰነድ ዝግጅት

- በበጀት አመቱ በግብርና ሚኒስቴር እና በግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲቲዊት በኩል የተዘጋጀው "**የባለብዙ ተዋንያን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትና አስተዳደር ረቂቅ**

**አዋጅ"** አዋጁ በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ቀርቦ ጸድቋል፡፡ አዋጁ የቁጥጥር ስርዐቶችን ያካተተ በመሆኑ በዝግጅት ሂደቱ ተሳትፎ በማድረግ አዋጁ እንዲዳብር ተደርጓል፡፡

- በበጀት አመቱ በግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲቲዊት በኩል የሚዘጋጀውን **"የግብርና ምርምር እና አገልግሎት ሰጪ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር ረቂቅ መመሪያ"** ዝግጅት ሂደት ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ለባለስልጣኑ ማናጅመንት፣ ለመሪ ስራ አስፈጻሚዎች እንዲሁም ለቴክኒካል ቡድን ረቂቅ መመሪያው ቀርቦ በተሰጠ ገንቢ አስተያየት እና አቅጣጫ መሰረት መመሪያው እንዲዳብር ተደርጓል፡፡
- በዓመቱ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር ረቂቅ መመሪያ እንዲሁም የግብርና መሳሪያ አምራች፣ ገጣጣሚ፣ አስመጪ እና ላኪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር ረቂቅ መመሪያዎችን ለማጸደቅ፤ የማብራሪያ ሰነድ የማዘጋጀት፣አስፈላጊ ሰነዶችን የማደራጀት፣ ከህዝብ እና ባለድርሻ አካላት በተለየም ከኢንደስትሪ ሚኒስቴር የተሰጡ አስተያየቶችን መሰረት በማድረግ መመሪያዎቹን የማበልጸግ ስራዎች ተሰርቷል፡፡ መመሪያዎቹ በህግ አስተያየት ዳብሮ እና የህግ ቅርጽ ይዞ እንዲጸድቅ ለሚመለከተው አካል ለመላክ በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

## 2. የዕጽዋት ምርትና ግብዓት ጥራት ቁጥጥር ዘርፍ

### 2.1 የፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ

**ፍቱንነቱ፣ደህንነቱ እና ጥራቱ የተረጋገጠ ፀረ-ተባይ**

- በበጀት ዓመቱ ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ ተረገግጠዉ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ፀረ ተባይ 121,579 ሜትርክ ቶን ታቅዶ 107,294 ተከናውኗል፣ አፈጻጸሙ 88.2% ነው፡፡
- ቅድመ የማስገቢያ ፈቃድ ጥያቄዎችን በመገምገም መስፈርቱት ሲያሚሉ ፍቃድ የተሰጠቸዉ 2425 ታቅዶ 2598 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸም 100+% በላይ የሆነበት ምክንያት የአገልግሎት ጥያቄ በመብዛቱ ነው፡፡

**ጥራቱ የተረጋገጠ ማዳበሪያ**

- በበጀት ዓመቱ ለ2441854 ሜ/ቶን ማዳበሪያ ጥራቱና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ታቅዶ 2089359 ሜ/ቶን (85.6%) የአፈር ማዳበሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ገብቷል፡፡
- በቁጥር ለ800 የቅድመ የማስገቢያ ፈቃድ ጥያቄዎችን በመገምገም መስፈርቱት ላሟሉ 871 (100+%) ፍቃድ የተሰጠ ሲሆን ክንውኑ ከፍ ያለው አገልግሎቱን የጠየቁ ተቋማት ቁጥር ከፍ በማለቱ ነው፡

**የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች**

- በበጀት ዓመቱ ለ295 የፀረ ተባይ እና ማዳበሪያ ተቋማት በመስፈርቱ መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ ለ 249 (84.4%) ተቋማት ብቃት ማረጋገጫ መስጠት ተችሎዋል፡፡

**በአካባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶችን በጥናት መቀነስ**

- በበጀት ዓመቱ 4 በአካባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶችን በጥናት መቀነስ የሚያስችሉ ጥናቶች ለማድረግ ታቅዶ 4ቱም ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙም (100%) ነው፡፡ በመሆኑም መስክ ቅኝቱ የተገኙ የፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ አጠቃቀም እና አያያዝ ስጋቶችን አስመልክቶ በቦታው ምክረ ሀሳብ የተሰጠ ሲሆን በቀጣይ ሊሰሩ የሚገቡ የስልጠና እና ናሙና በመውሰድ የሚሰሩ ስራዎች ተለይተዋል፡፡

**በመስክ ምርምር ፣ በዶዜር ግምገማ እና በቤተ-ሙከራ ፍቱንነቱ፣ ደህንነቱ ናጥራቱ ተረጋግጦ የተመዘገበ ፀረ-ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ**

- በበጀት ዓመቱ ለ445 ፀረ ተባይ እና ማዳበሪያዎች ፍቱንነት ፣የደህንነት እና ጥራትና በማረጋገጥ ለመመዝገብ ታቅዶ 497 (100+%) ተመዝግቦዋል፡፡ ክንውኑ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት የአገልግሎቶች ጥያቄ በመብዛቱ ነው፡፡

**የማዳበሪያ የኢትዮጵያ ደረጃን ሚሟላትን በተመለከተ**

- በሃገር ውስጥ የሚመረቱም እንዲሁም ከውጭ የሚመጡ 65 ማዳበሪያዎችን ናሙና በማሰባሰብ በላቦራቶሪ የማስፈተሽ ስራ የተከናወነ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 11 ምርቶች የምርመራ ውጤቱን ያለፉ ሲሆን 54 (83%) ምርቶች ሳያሟሉ በመቅረታቸው በመሆኑም የአዲስ ምዝገባ ወይም የምዝገባ እድሳት እንዳያገኙ ተደርጓል፡፡

**ቅንጅታዊ የቁጥጥር ስራ**

- የተቀናጀ የቁጥጥር ሥራን በተመለከተ፡ከአዲስ አበባ ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን፣ ከአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ እና ከአዲስ አበባ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ጋር በመቀናጀት በተከናወነው የቁጥጥር ሥራ፣ በሕገ-ወጥ የፀረ-ተባይ ንግድ ተግባር ላይ ተሰማርተው በተገኙ ነጋዴዎች ላይ ተገቢው የሕግ ማስከበር እርምጃ ተወስዷል።በዚህም መሠረት፣ በከተማው ውስጥ በፀረ-ተባይ ንግድ ላይ የተሰማሩ 139 ተቋማት ተለይተው የተመዘገቡ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 46 ተቋማት በኢንስፔክሽን ወቅት በአካል ተገኝተው ተመርመረዋል። በምርመራውም ወቅት የንግድ ቢሮ ባለሙያዎች በተገኙበት የማስጠንቀቂያ እና የእርምት እርምጃዎች ተወስደዋል።ከእርምት እርምጃ የተሰጣቸው ተቋማት ውስጥ 7 ተቋማት የተጠየቁትን የማስተካከያ እርምጃዎች ሙሉ በሙሉ አስፈጽመው ያስተካከሉ ሲሆን፣ 39 ተቋማት ደግሞ የተሰጣቸውን እርምት በማስተካከል ሂደት ላይ ይገኛሉ።በሌላ በኩል፣ 83 የሚሆኑ የፀረ-ተባይ ንግድ ተቋማት የንግድ ቦታቸውን ዘግተው ያልተገኙ በመሆናቸው ተገቢው የክትትል ሥራ በቀጣይነት እየተከናወነባቸው ይገኛል።

- ከግብርና ባለስልጣን እና ከኦሮሚያ ግብርና ግብዓቶች ቁጥጥር ባለስልጣን የተውጣጣ ቡድን በምስራቅ ሸዋ አካባቢ ባሉየግል እርሻዎች እና መደብሮች በመገኘት የፀረ-ተባይና ማዳበርያ አያያዝ እና አጠቃቀም ጋር ያሉ ሥጋቶች እንዲሁም ከፀረ-ተባይና ማዳበርያ ቁጥጥር ጋር በተያያዘ በአካባቢው ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በመፈተሸ ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ የማቅረብ ተግባር ተከናውኗል፤ እንዲሁም በችርቻሮ ሱቆች የተገኙ ያልተመዘገቡ ምርቶች ተሰብስበው በላቦራቶሪ እንዲመረመሩ የተደርገ ሲሆን በምርመራው ውጤት የተቀመጠውን የኢትዮጵያን ደረጃ ሳያሟሉ ቀርተዋል።

- በግብርና ምርምር ማዕከላት እና በዩኒቨርስቲዎች የተከናወኑ የአፈር ማዳበሪያዎች እና ፀረ-ተባይ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሚሰሩ ምርምሮች ያሉበትን ሁኔታ ለመገምገም በባለስልጣኑ ባለሙያዎች የመስክ ምልከታ በተለያዩ ቦታዎች ማለትም በጅማ የግብርና ምርምር ማዕከል፣ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ፣ በሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ተከናውኗል።

- ከአዲስ አበባ ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን፤ ከአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ እና ከአዲስ አበባ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ጋር በመቀናጀት በተከናወነው የቁጥጥር ሥራ፣ በሕገ-ወጥ የፀረ-ተባይ ንግድ ተግባር ላይ ተሰማርተው ለአከባቢም ይሁን ለጤና ስጋት የሚሆን ስራ ላይ በተገኙ 40 ነጋዴዎች ላይ ተገቢው የሕግ ማስከበር ሂደት ተከናውኗል።

- ከፀረ-ተባይ  አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ያሉ ስጋቶችን አስመልክቶ ጥናት(assesment) በአዲስ አበባ ከተማ የተመረጡ አከባቢዎች (ቦሌ፤ለሚ ኩራ፤አቃቂ ቃሊቲና ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተሞች) ላይ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተደዳር አርሶ አደር ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመሆን 69 ሄ/ር በሚሸፍኑ 29 አርሶ አደሮች ላይ ተሰርቷል፡፡ መሆኑ፡፡ በመሆኑም የፀረ-ተባይ አጠቃቀም እና አያያዝ ለአከባቢ እና ለጤና ስጋት ሊሆን እንደሚቸል የታየ ሲሆን ክፍተቶቹ እንዲስተካከሉ አዛው በመስክ ላይ ሙያዊ ምክረ-ሀሳብ የተሰጠ ሲሆን በቀጣይም ናሙና በመውሰድ ያለውን ተጨባጭ የስጋት ደረጃ ለመገምገም እየተሰራ ይገኛል፡፡
- የፀረ-ተባይ አስመጪ ተቋማት ላይ የፀረ-ተባይ አየያዝ፤ ሕጋዊ ሰነዶች እና አጠቀቃም ላይ ድንገተኛ ኢንስፔክሽን ሥራ ተሰርተው  ያሉ ክፍተቶችና ጠንካራ ጎኖች ላይ ምክረ አሳብ የቀረበ መሆኑ፡፡

## የሕግ ማቀፎች እና የደረጃ ዝግጅትን በተመለከተ

በ2018 ዓም በጀት ዓመት የቁጥጥር ሥራን ለማጠናከር በርካታ የሕግ ማዕቀፎች በሥራ አስፋፃሚው ተዘጋጅቷል፡፡

- በዚህም መሠረት የፀረ-ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር የፀረ-ተባይ ኢንስፔክሽንና የተቋማት ብቃት ማረጋገጫ ረቂቅ መመሪያ እና የፀረ-ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ 674/2002 ክፍተቶችን ለመለየት ጥናት ተደርጎ ፣ የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ እና የተሻሻለ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቶ ወደ ግብርና ሚኒስተር ለመላክ በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡
- የደረጃ ማሻሻያ እንዲደረግላቸው ጥያቄ የቀረበባቸውን የማዳበሪያ ደረጃዎችን ማለትም CES 68-2፡ 2018፣ES 408፡ 2006፣ CES 69-1፡ 2018፣ ES 3907-1፣ ES 3907-2፣ ES 3907-3፣ ES 3907-4  የማዳበሪያ ደረጃ ኮሚቴ 15 አባላት በጋራ በመሆን የማሻሻል ስራ ተሰርቷል
- የአፈር ማዳበሪያና ጤንነት ማሻሻያ ግብአት ምርት ግብይትና አጠቃቀም ቁጥጥር ረቂቅ  አዋጅን በተመለከተ ረቂቅ አዋጁን ከግብርና ትራንስፎርሜሽን ጋር በመተባበር ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ ባለሙያዎች ጋር በመሆን በድጋሚ የማሻሻል ስራ ተሰርቶ ለቀጣይ ምላሽ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን፡፡

- ደረጃ ሊዘጋጅለት ያልቻለው የባዮስቲሙላንት ማዳበሪያ የምዝገባ ጋይድላይን ዜሮ ድራፍት ተለያዩ መድረኮች ለባለድርሻ አካላት በመጀመሪያ፣ በመቀጠልም ለዘር ተመራማሪዎች ቀርቦ እንዲተች ተደርጎ መወሰድ ያለባቸው ግብዓቶችን በማካተት የመጨረሻው ጋይድላይን ተዘጋጅቶ እና ፀድቆ ለሬጉላቶሪ ስራው እየዋለ ይገኛል፤
- የስነ-ህይወታዊ ፀረ-ተባይ ምዝገባ መመሪያ ወደ ፍትህ ሚኒስቴር እንዲላክ ለግብርና ሚኒስትር ቢላክም ከግብርና ሚኒስትር ህግ ክፍል ማሻሻያ እንዲደረግበት በመወሰኑ ከግብርና ሚኒስትር ህግ ክፍል ባለሞያዎች ባሉበት ዳግም ውይይት ተደርጎ ረቂቅ መመሪያውን በመከለስ ዳግም ወደ ግብርና ሚ/ር ለመላክ እየተሰራ ነው፡፡

**የአቅም ግንባታ እና ስልጠና**

- ሁለት ባለሙያዎች ወደ ህንድ ሀገር ለሁለት ሳምንት አጭር ስልጠና አግኝተው ተመልሰዋል፡፡
- ለክልል ግብርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ቢሮዎች፣ ከኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ማዕከል እና ከቅርንጫፎች ለተወጣጡ 37 ሰልጣኞች በፀረ-ተባይ እና የማዳበሪያ ሬጉላቶሪ አሰራር እና ተያያዥ ሕግ ማቀፎች ላይ ሥልጠና ተሰቷል፡፡

**ለፖሊስ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ**

- ከኦሮሚያ ክልል ፖሊስ መምሪያ የወንጀል ምርመራ ዋና ክፍል በአካባቢው ሲዘዋወሩ የተያዙ ፈሳሽ ማዳበሪያዎችን በተመለከተ የብቃት ማረጋገጫ ዕድሳት እና ምዝገባ በተመለከተ በተለያየ ጊዜያት ለቀረቡ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

- ለኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ "Proper 360 SL /HERBICIDE/ "የተባለውን የፀረ-አረም አስመልክቶ በቀረበው ጥያቄ መሰረት ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

## 2.2 ጤንነቱ፣ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች

ጤንነቱ፣ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች

- በአጠቃላይ በዚህ ዓመት ወደ ውጪ ለሚላኩ የጥራጥሬ፣ የቅባት፣ የዕህል፣ የቡና፣ የአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ቅመማቅመም ምርቶች ላይ የኢንስፔክሽን ሥራ ለማከናወን 960,000 ቶን ታቅዶ፣ ዕቅዱን 117% በማሳካት 1,127,665 ቶን ምርት

ተመርምሮ ተልኳል። የከፍተኛ አፈጻጸም ምክንያት፦ የሀገር ውስጥ ምርት መጨመር እና በዓለም አቀፍ ገበያ የተቀባይ ሀገራት ፍላጎት ከፍተኛ መሆን።

- በዚህ ዓመት ወደ አሜሪካ የሚላኩ የአበባ ቁርጥራጭ (Pelargonium) ምርቶች በአሜሪካ ኦዲተሮች በተደረገባቸው ጥብቅ የኦዲት ፍተሻ ውጤት መሰረት ለ2025/2026 ምርት ዘመን ወደ አሜሪካ ገበያ ለመላክ የሚያስችል ይፋዊ ሰርተፊኬት ማግኘት ተችሏል። በዚህም እርሻዎቹ ምርታቸውን በአግባቡ እንዲልኩና የገበያ ተደራሽነቱ እንዲሰፋ ተደርጓል።
- በዚህ ዓመት ወደ አውሮፓ ህብረት የሚላኩ የሮዝ አበባ አምራች ላኪዎች በFalse Codling Moth (FCM) መቆጣጠሪያ ሰነድ (System Approach Document) መሠረት መስራቱን በአውሮፓ ኦዲተሮች የስራ ክፍሉ/በብሔራዊ የዕፅዋት ጥበቃ ድርጅት (NPPO)/ ተገምግሞ ያለምንም የቴክኒክ ክፍተት (ግብረመልስ) ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አግኝቶ የኤክስፖርት ንግዱ ያለ ምንም እገዳ እንዲቀጥል ተደርጓል።
- በዚህ ዓመት ከእርሻዎችና ከተለያዩ አካባቢዎች የተሰበሰቡ ናሙናዎች በሆለታ ብሔራዊ የግብርና ባዮቴክኖሎጂ ምርምር ማዕከል በ PCR ምርመራ ተደርጎ ኢትዮጵያ ከ Xylella fastidoisa ባክቴሪያ ነፃ መሆኗ በላብራቶሪ ተረጋግጧል። በዚህም ስድስት (6) ትልልቅ እርሻዎች ምርታቸውን ወደ ዓለም ገበያ እንዲልኩ ተደርጓል።

**ጤንነቱ፣ ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች፣**

- ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ዉጤቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁስ ላይ በዚህ 12 ወር 65,000 ቶን የኢንስፔክሽን ሥራ ለመስራት ታቅዶ ክንውን 274,875 (>100 %) ቶን የኢንስፔክሽን ሥራ በማከናወን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል። ለአፈጻጸም ከፍተኛ መሆን ለጋሽ ድርጅቶች ለእርዳታ እና አምራች ድርጅቶች ለኢንድስቱሪ ግብዓትነት የሚውል ከውጭ እንዲገባ በመፈቀዱ ነው።
  - በዚህ ዓመት የድህረ-መግባት ኳራንቲን (Poቋst-Entry Quarantine/PEQ/ ማለፍ ያለባቸውን ዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤት ለመከታተል 6 ታቅዶ 6ቱ ላይ (100%) ሙሉ ክትትል ተደርጓል። የተወሰደ ልዩ እርምጃ (Case Study)፦ ከኬንያ በሞያሌ መስመር ለእርዳታ የገባ የማሽላ ምርት የአገሪቱን መስፈርት

አሟልቶ ባለመግባቱ በሆለታ ብሔራዊ ምርምር ማዕከል ጥብቅ የላብራቶሪ ምርመራ እንዲደረግበት ተደርጓል። ምርቱ ከኳራንቲን ተባይ ነፃ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጓል።

**የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች**

- በዚህ 12 ወር አጠቃላይ በገቢና በወጭ የዕፅዋት ምርቶች ላይ አዲስ እና እድሳት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት 678 በቁጥር ታቅዶ 246 (36%) መስጠት ተችሏል። ለአፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን በዚህ ዓመት ለስራ ክፍሉ የቀረበ የብቃት ማረጋገጫ  የእድሳት ጥያቄ ዝቅተኛ መሆን እና በተለይ አስመጪዎች የስራ ዘርፍ መቀየር ለአንድ ጊዜ ብቻ ብቃት ማረጋገጫ መውሰድና ማቋረጥ በዘርፉ አለመቀጠል የእድሳት ቁጥር እንዲቀንስ አድርጎታል።

**ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (Digitalization) የታገዘ አገልግሎት**

- የePhyto ሥርዓትን ከብሔራዊ የአንድ መስኮት አገልግሎት (ESW)፣ ከቴሌብር እና ከአለምቀፉ የIPPC HUB ጋር የማስተሳሰር (Integration) እና የማረጋገጥ (Validation) ስራ ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል። ለትግበራው መሳካት ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር የመግባቢያ ሰነድ (MoU) የተፈረመ ሲሆን፣ በ6 የተመረጡ የአበባ ላኪ ድርጅቶች ላይ የሙከራ (Pilot) ስራውን ለማስጀመር የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ይገኛል። ይህ ስራ የወጪ ንግድ ፍቃድ አሰጣጥን ይበልጥ ደህንነቱ የተጠበቀ ፈጣንና አለምቀፍ መስፈርትን ያሟላ በማድረግ የወረቀት ስራንና የአሰራር መጓተትን ያስቀራል። ከቴሌብርና ከጉምሩክ ጋር መተሳሰሩ ደግሞ የክፍያና የቁጥጥር ሂደቱን በአንድ ማዕከል በማስተሳሰር ለላኪዎች ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።
- የዕፅዋት ኳራንታይን አገልግሎትን ይበልጥ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ዲጂታላይዝድ ለማድረግ በተደረገው ጥረት፣ በTMA የበጀት ድጋፍ 18 ላፕቶፕ (Laptop)፣ 15 ታብሌት (Tablet)፣ 3 ዴስክቶፕ ኮምፒውተሮች (Desktop Computers)፣ 2 ፕሪንተሮች (Printers) እና 3 ዩፒኤስ (UPS) የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች ተገዝተው ለሥራ ክፍሎች ድጋፍ ተደርጓል።ይህ የቴክኖሎጂ ድጋፍ በየጣቢያዎቹ የሚገኙ

የዕፅዋት ኳራንታይን ኢንስፔክተሮች በመስክ ላይ ሆነው የኢንስፔክሽን ሪፖርቶችን በኤሌክትሮኒክ መንገድ በቀጥታ እንዲያስተላልፉ እና በቦታው ላይ የዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቶችን (Phytosanitary Certificates and Import authorization) እንዲሰጡ አቅም የፈጠረ ሲሆን፣ በተጨማሪም የአገልግሎት አሰጣጡን ፍጥነት፣ ቅልጥፍና፣ ግልጽነት እና ተደራሽነት በእጅጉ አሻሽሏል።

- በበጀት ዓመቱ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አሰጣጥ አገልግሎትን ሙሉ በሙሉ ዲጂታላይዝ በማድረግ፣ በመሶብ (MESOB) ፕሮግራም/ስርዓት በኩል አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል። የአገልግሎቱ ሙሉ በሙሉ ወደ ዲጂታል መድረክ መሸጋገር የአገልግሎት ፈላጊዎችን እንግልት ከመቀነሱም በላይ የሰርተፊኬቶችን/ሰነድ ትክክለኛነትና ተአማኒነት በማረጋገጥ ረገድ የጎላ ድርሻ አለው።

**የተጠናከረ የህግ ማዕቀፍ ተፈጻሚነት**

- የዕፅዋት ጥበቃና ኳራንቲን አዋጅ በግብርና ቋሚ ኮሚቴ የተሰጡ አስተያየቶች ተካተውበትና ማብራሪያ ተሰጥቶበት በዚህ ዓመት እንዲጸድቅ ተደርጓል። የአዋጁ መጽደቁ የሀገሪቱን የኳራንቲንና የዕፅዋት ጥበቃ ቁጥጥር ሥርዓት ከዓለም አቀፍ አሰራሮች ጋር በማጣጣም የግብርና ምርት ወጪ ንግድን (Export) በከፍተኛ ደረጃ ያሳድጋል።

- የዕፅዋት ምርት ጥራትና ደህንነት አዋጅ፦ የዜሮ ድራፍት (Zero Draft) አዋጅ እና ጥናታዊ መነሻ ፅሑፍ ለበላይ አመራር ቀርቦ እንዲሰራ ጸድቋል። የቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሞ ከአውሮፓ የህግ ማሕቀፍ ተሞክሮዎችን ለማካተት ከTwining Fiche ፕሮጀክት ከፍተኛ ባለሙያዎች ጋር የሁለት ቀናት የጋራ ግብዓት የማበልጸግ ስራ ተከናውኗል። የአውሮፓን ተሞክሮ ያካተተ ጠንካራ የህግ ማዕቀፍ መዘርጋቱ ወደ አውሮፓ ህብረት የሚላኩ የግብርና ምርቶች ላይ የሚጥሉ የጥራትና ደህንነት ዕገዳዎችን (Interceptions) አስቀድሞ ለመከላከል ያስችላል።

- በዚህ ዓመት የተዘጋጁ 5 የዕፅዋት ተባይ ትንተና እና አሰሳ ጥናታዊ መረጃዎች በቴክኒካል ቡድኑ በድጋሚ ታይተው ለህትመት ዝግጁ እንዲሆኑ ተደርጓል። እነዚህን የPRA ሰነዶች ማተም የሀገሪቱን የባዮ-ሴኪውሪቲ (Biosecurity) አቅም የሚያጠናክር ሲሆን በዓለም አቀፍ ንግድ ወቅት በሳይንሳዊ መረጃ ላይ የተመሰረተ ድርድር ለማድረግ ወሳኝ ማስረጃ ሆኖ ያገለግላል።

- በዚህ ዓመት የPRA Operational Procedure የመጀመሪያው ረቂቅ (Draft) ሰነድ ተዘጋጅቷል። ይህ ሰነድ ሲጠናቀቅ የተባይ ስጋት ግምገማዎች ወጥ፣ ግልጽ እና ደረጃቸውን የጠበቀ አግግሎት ለመስጠት ያስችላል።

- በዚህ ዓመት የSystem Approach ሰነድ (ለአውሮፓ አበባ ኤክስፖርት)፦ በትግበራ ወቅት የሚያግዙ 4 የአሰራር ሥርዓቶች /ቋoP በTMA በጀት ድጋፍ እና በCABI ከፍተኛ ባለሙያዎች እገዛ ተዘጋጅተዋል (3ቱ አዲስ ሲሆኑ፣ 1ዱ ማሻሻያ የተደረገበት ነው)። ይህ ሰነድ በአበባ ምርቶች ላይ False Codling Moth (FCM) ስጋትን ለመቀነስ ለባለሙያው ግልጽ የሆነ ሰነድ ነው።

- በዚህ ዓመት በአውሮፓ ገበያ ላይ የተጣለውን ጥብቅ የኳራንቲን መስፈርት ለማሟላትና በአበባ ምርቶች ላይ የFalse Codling Moth (FCM) ስጋትን በዘላቂነት ለመቀነስ 4 የአሰራር ሥርዓቶችን (SoPs) በTMA (TradeMark Africa) የፋይናንስ ድጋፍ እና በCABI ከፍተኛ ባለሙያዎች እገዛ በዚህ ዓመት ማዘጋጀት ተችሏል። ይህ ሰነድ በተግባር ላይ የሚገኙ ባለሙያዎች ስራቸውን በግልጽና በወጥ መንገድ እንዲያከናውኑ የሚያግዝ ሰነድ መሆኑ ተረጋግጧል።

- በዚህ ዓመት የካሳቫ/cassava/ እና የሶያሚል/Soyameal/ ምርትን ወደ ቻይና ለመላክ ፕሮቶኮል ተፈርሟል። ይህ ስምምነት የኢትዮጵያን የግብርና ምርት የወጪ ንግድን በጥቂት ምርቶች ላይ ብቻ እንዳይወሰን /Diversify/ ለማድረግ በር ይከፍታል።

- በዚህ ዓመት የLocal Ethio-GAP ሰነድ ተጠናቆ ቫሊዴት (Validate) ተደርጓል። የአገር ውስጥ አምራቾች ዓለም አቀፍ የመልካም አመራረት ልምዶችን (Global-GAP) ማሟላት እንዲችሉ እንደ መሸጋገሪያ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል።

- በበጀት ዓመቱ በስራ ክፍሉ የሚዘጋጁ የህግ ማህቀፎች ተለይተው ለህግ ክፍል ተልከዋል። የህ አሰራር የቁጥጥር ስራዎች በህግ የተደገፉ እና ግልጽነት ያላቸው እንዲሆኑ በማድረግ ተጠያቂነትን ያሰፍናል።

- በዚህ ዓመት የስራ ክፍሉን ስራዎች ለማገዝ የሚያስችሉ የGIZ & FAO/STDF የፕሮጀክት ፅንሰ-ሀሳብ ተቀርፆ በጀት እንዲፈቀድ የክትትል ስራ ተከናውኖዋል። ይህ ፕሮጀክት የመንግስትን ውስን በጀት በቀጥታ ከመጠባበቅ ይልቅ፣ ከዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች

ተጨማሪ የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ በማግኘት የሥራ ክፍሉን ዕቅዶች ለማስፈጸም ያስችላል፡፡

**የተሰጠ አቅም ግንባታ**

- በዚህ ዓመት በCABI ከፍተኛ ባለሙያዎች የታገዘ የሁለት ዙር የአሰልጣኞች ስልጠና (ToT) ለኳራንታይን ባለሙያዎችና ለሥራ መሪዎች ተሰጥቷል፡፡ የተገኘ ውጤት ፦ የባለሙያዎች የFCM ተባይን የመለየት እና ጥብቅ የቁጥጥር ሥርዓት የመዘርጋት አቅም በከፍተኛ ደረጃ አድጓል፡፡ በተጨማሪም ቀልጣፋ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት በመዘርጋቱ፣ ወደ አውሮፓ ህብረት (EU) የሚላኩ የአበባ ምርቶች የኳራንታይን መስፈርትን እንዲያሟሉ በማድረግ ከዚህ ቀደም በተባይ ምክንያት ይቀርቡ የነበሩ ዓለም አቀፍ ቅሬታዎችና እገዳዎች (Interceptions) በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀነሱ ተደርጓል፡፡
- በዚህ ዓመት የስራ ክፍሉ ሰራተኞች የ5 million data Encoder ሥልጠና እንዲወስዱ ክትትል ተደርጓል፡፡
- በዚህ ዓመት የስራ ክፍሉ ባለሙዎች እና የጣቢያ ኢንስፔክተሮች በCOLEAD e-learning Program በበየነ መረብ የሚሰጠውን ሥልጠና በመውሰድ እራሳቸውን በማብቃት የተለያዩ ሰርተፊኬቶችን ማግኘት ችለዋል፡፡
- በዚህ ዓመት 2 የዕፅዋት ተባይ ስጋት ትንተናና አሰሳ ዴስክ ኃላፊ እና ባለሙያ ለ5 ቀን ኬንያ በመሄድ ለስራ ክፍሉ የሚያግዙ ልምዶችን እንዲቀስሙ ተደርጎል፡፡ ውጤት
- በዚህ ዓመት ከግብርና ሚኒስትር ጋር በጋራ የምግብ ደህንነት እና ጥራት የማሰልጠኛ ማንዋል፣ ፕርዘንቴሽን እና ፋሲሊቴተር ጋይድላይን ተዘጋጅቶ ለክልል እና ለተመረጡ ባለሙያዎች በምግብ ጥራት እና ደህንነት ቁጥጥር ላይ ToT ሊሰጡ የሚችሉ 8 ባለሙያዎች ከባለስልጣን መስሪያቤቱ በተዘጋጀው ዶክመንት ላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል፣ ስልጠናም ተሰጥቷል፡፡
- በዚህ ዓመት የስራ ክፍሉ ዴስክ ሃላፊ የተቋሙን የሪፎረም ኮሚት አባል በመሆን አጠቃላይ የሪፎርም ስራዎችን እንዲሁም ለተቋሙ ሰራተኞች በሪፎረሙ ዙሪያ ስልጠና መስጠት ላይ ተሳትፎ ተደርጎል፡፡

**ሌሎች ተጨማሪ የተሰሩ ስራዎች**

❖ በዚህ ዓመት High-Level Regional SPS Conference በማካሄድ፡

- ተቋሙን እና በስራ ክፍሉ የሚሰጡ አገልግሎቶችን የማስተዋወቅ ሥራ ተሰርቷል፣
- ተቋምን እና የሥራ ክፍሉን ሲደግፉ የነበሩት መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ ኢንባሲዎች እና የግል ባህብቶች እውቅና የተሰጠበት መድረክ ተካሄዷል፣
- አብሮ የመስራት፣ የመተባበር፣ የመቀናጀት እና የተለያዩ ልምዶችን የተቀሰሙበት መድረክ እንደሆነ ተለይቷል፣
- በአህጉራዊ እና በዓለማቀፋዊ ደረጃ ትብብርን ለማሳደግ እና አቅምን ለማጎልበት ዋና ቁልፍ መድረክ እንደሆነ ታይቷል፡፡

➢ በዚህ ዓመት ወደ አውሮፓ ለሚላከው የቃሪያ ምርት በኦልቲካለቸር ባህበር የበጀት ድጋፍ ቋyቋtem approach Document ተዘጋጅቷል፡፡

➢ በዚህ ዓመት በ False Codling Moth (FCM) ተባይ ምክንያት ተቋርጦ የነበረውን የሮዝ አበባ ወደ ደቡብ ኮሪያ ኤክስፖርት ለማስቀጠል፣ ከባለስልጣኑ፣ ከግብርና ሚኒስቴር እና ከማህበሩ የተወከለ ልዑክ በደቡብ በኮሪያ ባደረገው ውይይት በ System Approach ሰነድ እና ተጨማሪ መስፈርቶች ላይ ስምምነት ላይ ደርሷል፡፡ በዚህም መሰረት ሀገራችን ተባዩን የምትቆጣጠርበትን ዝግጁነት ለማረጋገጥ በደቡብ ኮሪያ ባለሙያዎች የሚደረገውን ኦዲት (Audit) ለማካሄድ ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡

➢ በዚህ ዓመት የስራ ክፍሉን የአገልግሎትና የአገልግሎት ስነ-ምድብ / Service Taxonomy፣ የአገልግሎት ስታንዳርድ / Service standard፣ የአገልግሎት ፍሰትና ማፒንግ / Workflow and Service ProceSS Mapping እና የአገልግሎት ካታሎግ / Service Catalogue ተሰርቷል፡፡

➢ በዚህ ዓመት በስራ ክፍሉ በPCE TOOL የተዩ ክፍተቶች መሰረት ያደረገው የ 5 ዓመት እስትራትጂክ እቅድ ጸድቆ የመጨረሻው ሰነድ ህትመት ላይ ነው፡፡

➢ በዚህ ሩብ ዓመት የTwining Fiche Work plan ተዘጋጅቷል፡፡

➢ በዚህ ዓመት የስራ ክፍሉ እና የጣቢያ ባለሙዎች COLEAD ሥልጠና እንዲያገኙ Action plan ተዘጋጅቶ ተልኳል፡፡

➢ በዚህ ዓመት በመንገደኛ ለሚገቡና ለሚወጡ የዕፅዋት ምርት ላይ ፍተሻ እንዲካሄድ

የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ላይ ክትትል ተደርጎል፡፡

- በዚህ ሩብ ዓመት የephyto ኤሌክትሮኒክስ ሲስተምን በሙከራ ደረጃ ለመተግበር ከአበባ እርሻ ላኪዎች ለመጡ ባለሙያዎችና ለቦሌ የባለስልጣኑ ባለሙያዎች አስፈላጊው ስልጠና ተሰፀቷል፡፡
- በሆርቲፍሎራ እና በሆርቲካልቸር አሶሴሽን የተዘጋጀውን የሆርቲካልቸው ኤግዚብሽን ስራ ተሰቷል፡፡
- በዚህ ሩብ ዓመት ዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤት ከብራዚል ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ የመግባቢያ ሰነዶች ላይ አስተያየት ተሰቶል
- የኢትዮጵያ የምግብ እና ስርዓተ ምግብ ሽግግርን ለማጠናከር የሚያስችል ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

## 2.3 በላቦራቶሪ የጥራት ፍተሻ የተደረገላቸው የ ዕጽዋት ዘር፣ ምርትና የ ዕጽዋት ውጤቶች

- የዕጽዋት ምርትና ግብዓት ላቦራቶሪ በዓመቱ 300 እንዲሁም አረተኛ ሩብ ዓመት ደግሞ በ80 የተለያዩ የአትክልትና የሰብል ዘር ናሙናዎች ላይ የላብራቶሪ የዘር ጥራት ፍተሻ ለማከናወን እና ውጤት ለማሳወቅ ታቅዶ 91 ለጥራት ፍተሻ ላቦራቶሪው የቀረበው የናሙና ብዛት 330 (110%) የተለያዩ የአትክልት እና የሰብል ናሙናዎች ላይ የጥራት ፍተሻ ስራ ተከናውኗል፡፡
- በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ከክልል በሚመጡ 300) የተለያዩ የሰብል ወይም የአትክልት ዱፕሊኬት (Duplicate) የንጽጽር ናሙናዎች ላይ የንጽጽር የላብራቶሪ ፍተሻ ስራዎች ለማከናወን ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በሩብ አመቱ በ330 የንጽጽር ናሙናዎች ላይ የላብራቶሪ ፍተሻ ስራ ተከናውኗል፡፡
- 4ተኛ ሩብ ዓመት በ40 ወደ ውጭ በሚላኩ የዕጽዋት እና የዕፅዋት ውጤት ናሙናዎች ላይ የጥራትና ደህንነት የላቦራቶሪ ፍተሻ ለማከናወን ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በሩብ አመቱ በ66 ናሙናዎች ላይ የጥራትና ደህንነት ፍተሻ ስራ ተከናውኗል፡፡ ይህም በመቶኛ (165%) ነው፡፡ አፈጻጸሙ ከመቶ ፐርሰንት በላይ የሆነበት ምክንያት ለፍተሻ ወደ ላቦራቶሪው የቀረበው የናሙና ብዛት ከፍ በማለቱ ነው፡፡
- 4ተኛ ሩብ ዓመት በ20 ወደ አገረ ውስጥ በሚገቡ የእጽዋት እና የእፅዋት ውጤት ናሙናዎች ላይ የጥራትና ደህንነት የላቦራቶሪ ፍተሻ ለማከናወን ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በሩብ አመቱ በ26ናሙናዎች ላይ የጥራትና ደህንነት ፍተሻ ስራ ተከናውኗል፡፡ ይህም

በመቶኛ (130%) ነው፡፡ አፈጻጸሙ ከመቶ ፐርሰንት በላይ የሆነበት ምክንያት ለፍተሻ ወደ ላቦራቶሪው የቀረበው የናሙና ብዛት ከፍ በማለቱ ነው፡፡

### 2.4 የዕጽዋት ዘርና ዝርያ ቁጥጥር

- ከውጪ የመጣ ናሙና በቁጥር ሁለት( Beetroot/ Detroit Dark Red መጠን 14,000kg and also one Vegetable Sweet Pepper/ Austin 0.5kg not accepted.)ተቀባይነት አላገኘም፡፡
- በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ የአገር ውስጥ ዘር ከዓመቱ እቅድ ጋር ሲነጻጸር አፈጻጸሙ ዝቅ ሊል የቻለው የብጠራ ስራው ገና እየተከናወነና ያልተገባደደ ስለሆነ ነው፡፡
- ለ30 አዲስ በዘር ስራ የተሰማሩ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅደ ለ 31 (103%) አዲስ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ መስጠት ተችሏል፡፡
- ለ120 በምርምር የቀረቡ ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎችን ግምገማ ለማካሄድ ታቅዶ 127 (106%) እጩ ዝርያዎች ቀርበው በመስክ ተገምግሟል፡፡
- ጥራትና ዉጤታማነታቸው ተረጋግጦ የሚለቀቁ የዕፅዋት ዝርያዎች 78 ታቅዶ 92 (118%) ነው፡፡
- በቁጥር 300 ከውጪ የገባ ዘር ናሙና ጥራቱ በላብራቶሪ እንዲፈተሽ ለማድረግ ታቅደ 330 (110%) የተከናወነ ሲሆን ይህም የናሙና ዕቅድ 400,000 ኪ.ግ ሊወክል እንደሚችል ታሳቢ ቢደረግም 402,715 ኪ.ግ የዕቅዱን (81%) ሊሆን ችሏል፡፡ አፈጻጸሙ አነስተኛ የሆነው ናሙናዎቹን ይወከላል ተብሎ የተገመተው የዘር መጠን (Actual lot size) አነስተኛ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡
- 14ኛው ዙር ሀገር አቀፍ የዘር ጥራት ቁጥጥር መድረክ የሬጉላቶሪ ስርዓት ከዘረጉ ሁሉም ክልሎችና ሁለቱ የከተማ መስተዳደሮችን ጭምር በማካተት የተደረገ የእስካሁን አፈጻጸም ቀርቦ ተገምግሟል፣ ስምምነት የተደረሰባቸው የቀጣይ ትኩረት አቅጣጫ ተለይተዋል፡፡
- የክልሎችን አፈጻጸምና መረጃ በዙም ስብሰባ በማድረግ በየ15 ቀኑ የመገምገም ስራ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡
- አስፈላጊ መረጃዎችን በማሰባሰብ የዝርያ መዝገብ መጽሐፍ ህትመት 27 ተጠናቆ በአርድ ኮፒና በሶፍት ኮፒ ተዘጋጅቷል፡፡

- የፍራፍሬ ችግኝ የጥራት ቁጥጥር ስራ፣ የችግኝ ጣቢያ እና የፍራፍሬ የትራት ደረጃዎች መስፈርትን በሚመለከት በየክልሉ ለሚገኙ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ከግብርና ሚንስቴርና ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት የግንዛቤ ማስጨበጫ ለሶስተኛ ጊዜ ተሰጥቷል፡፡
- የአትክልት ዘር የጥራት ፍተሻ የበሽታ ልየታ ለኢንስፔክሽን ባለሙያዎች ከግብርና ሚንስቴርና ከአጋር ድርጅቶች ጋር
በመቀናጀት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በዘር ናሙና አወሳሰድ ላይ ለኢንስፔክሽን ባለሙያዎች በሁለት ዙር ተግባር ተኮር ስልጠና ባለሙያዎች ተሰጥቷል፡፡
- ወደ መሶብ ሊገቡ የሚችሉ ተጨማሪ 8 በድምሩ 15 አገልግሎቶችን ከMINT/Perago ጋር በጋራ ተሰርቶ ለአገልግሎት ተመቻችቷል፡፡
- ለራስ አገዝ እና ለሶስተኛ ወገን ዘር ጥራት ማረጋገጥ ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር መመሪያ እና የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርት የማያሟላ የዕጽዋት ዘር አጠቃቀም እና አወጋገድ መመሪያ አስፈላጊውን ሄደት በማለፍ የጸደቀ ሲሆን በፍትህ ሚንስቴር የመመሪያ ቁጥር እንዲሰጠው ተልኳል፡፡
- የህገ - ወጥ ዘር ጥራት ቁጥጥር ረቂቅ መመሪያ ከግብርና ሚንስቴር ጋር በመሆን ተዘጋጅቷል፡፡
- ክግብረና ትራንስፎርሜሽን ኢንስትቲዩት ጋር በመነጋገር በዘር ላይ ያሉ ዲጂታል ስራዎች ህገ-ወጥ ዘርን ለመከላከል የመለያ ምልክትና የዘር ሰርተፊኬሽን ትራኪንግ ሲስትም ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡
- ከባለስልጣኑ የህግ አገልግሎት እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኪሚሽንጋር በመቀናጀት ችግሩ በሚስተዋልባቸው ክፍለ ከተሞች (አረዳ እና አዲስ ክፍለከተሞች) እንደሁም በአዲስ አበባ ዙሪያ ሕገ - ወጥ የዘር ጥራት ንግድ ላይ የመስክ ቅኝነት ተደርጎ አስፈላጊውን የግንዛቤና የማስተካከያ እርምጃ ተወስዷል፡፡ እንደክፍተት በታዩ፣ ዘርን ከሌሎች የግብርና ግብዓቶች ጋር በአንድ መሸጫ ክፍል ውስጥ መደርደር፣ የአሀገር ውስጥ ዘሮችን በአንድ ላይ አጭቆ ለሽያጭ ማቅረብ፣ የዘር ቅብብሎሽ ላይ መረጃ ለመስጠት ፍቀደኛ አለመሆን፣ የመሳሰሉት ተገኝተዋል፣ የቃልና የጽሁፍ ማስጠንቀቂያዎች ተሰጥተዋል፡፡

### 3 የእንስሳት ግብዓቶች ምርቶች እና አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር

### 3.1የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ

- በአጠቃላይ በበጀት አመቱ 25,000 ቶን ሥጋ እና ተረፈ ስጋ ምርት ለማምረትና ለመላክ ታቅዶ በድምሩ 19,594.635 ቶን ስጋ እና ተረፈ ስጋ ምርት ተልኳል፡፡የእቅዱ አፈፃፀም 78.4% ነው፡፡ ለዚህ በምክንያትነት የሚገለጸው የሀገራችን የስጋ ምርት 60% በማስገባት የምትታወቀው UAE በመካከለኛው ምስራቅ በነበረው ጦርነት ምክንያት በረራዎች መሰረዛቸው በኤክስፖርቱ ላይ ተፅዕኖ በመፍጠሩ ነው፡፡
- **በአጠቃላይ በበጀት አመቱ የቅድመ ዕርድ ምርመራ የተደረገላቸው የቁም እንስሳት** በዓመቱ **2.7** ሚሊዮን እንሰሳት የቅድመ ዕርድ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ በድምሩ **2.379666** ሚሊዮን ተከናውኗል፡፡ ይሄም የእቅዱ **88.14 %** ነው፡፡በአጠቃላይ **6,556** (<1%) እንሰሳት በቅድመ እርድ ምርመራ ውድቅ የተደረጉ ቢሆንም ይህም ከጊዜ ወደ ጊዜ በተደረገው የኢንሰፔክሽን ስራ እየቀነሰ ቢመጣም ወድቅ ለተደረጉት እንሰሳት ዋነኛ ምክንያታቸው

  - የእንስሳት ክብደት ትልቅ መሆን እና ከሚፈለገው መጠን ማነስ
  - ሲጓጓዙ የእንሰሳት የሰውነት መጉዳት፣
  - የበሽታ ምልክት መታየት፤

- **የድህረ ዕርድ ምርመራ የተደረገላቸው የታረዱ እንስሳት**

  - በአጠቃላይ በበጀት አመቱ **2.69** ሚሊዮን እንስሳት የድህረ ዕርድ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ **2.01821** ሚሊዮን ተከናውናል፡፡ ይህም የእቅዱ **75.03%** ተከናውኗል፡፡ በድህረ እርድ ምርመራ ከተመረመሩት ውስጥ **10,386** (<1%) ውድቅ ተደርጓል፡

  - የእንሰሳት ምርቶችን ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ ሥጋና  ተረፈ ሥጋ ምርት ተመርቶ ለውጭ ገበያ እንዲላክ የኢንስፔክሽ አገልግሎት በመስጠት፣የቅድመ ዕርድና ድህረ እርድ ምርመራ በማከናወን እና የቄራዎችን ሀይጅንና ሳኒቴሽን እንዲጠበቅ በመቆጣጠር ጤንነቱ ፣ደህንነቱና ጥራቱን የጠበቀ ለወጭ ገበያ የሚቀርብ እና ለሰው ምግብነት የሚውል የስጋ ምርት እንድመረት ማስቻል ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በላቦራቶሪ

ምርመራ የስጋ ደህንነት እንዲረጋገጥ በማድረግ ለኤክስፖርት ብቁ የሆነ ሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት በማምረት፣

- **በ4ኛ ሩብ** 180 ናሙናዎችን ለመሰብሰብና ለመመርመር ታቅዶ 122 (67.8%) ናሙናዎች ላይ የላቦራቶሪ ፍተሻ ተካሂዷል፡፡ ነገር ግን በበጀት ዓመቱ ለማካናወን የተቀመጠውን ግብ ሙሉ በሙሉ ማሳካት ተችሏል፤በአጠቃላይ 730 የእንስሳት ምርት ናሙናዎችን ለመመርመር ታቅዶ 734 (100.5%) ናሙናዎች ላይ የላቦራቶሪ ምርመራ ተግባራት ተከናውኗል፤ዝርዝር አፈጻጸሙ እንደሚከተለው ቀርቧል፤፤

- በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ለ91 ለኮመርሻል የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ ለ 90 የብቃት ማረጋገጫ የጠሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙም 98.% ነዉ፡፡
- የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ ሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት ተመርቶ ለውጭ ገበያ እንዲላክ 60 የኢንስፔክሽን አገልግሎት ለመስጠት፣ ታቅዶ 60 (100 %) ኢንስፔክሽን ለማከናወን ተችሏል፡፡

**የሥጋ እና የጥሬ ወተት የመድኃኒት ቅሪት (Drug Residue) ፍተሻ አፈጻጸ**

- በላቦራቶሪ ከተመረመሩት 70 ናሙናዎች መካከል 16 (22.9%) ላይ የጸረ-ተህዋስያን (አንቲባዮቲክስ) መድኃኒት ቅሪት መኖሩ ተረጋግጧል። ይህ ግኝት እንስሳቱ በመድኃኒት ከተከሙ በኋላ ምርታቸው ለገበያ ከመቅረቡ በፊት ሊጠበቅ የሚገባው የእገዳ ጊዜ (Withdrawal Period) በአግባቡ እየተከበረ አለመሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ጥብቅ የቁጥጥር ስራን ይሻል።
- **የጥሬ ወተት አልሚ ምግብ ይዘት (Milk Nutritional Content) ምርመራ አፈጻጸም**

የጥሬ ወተት ንጥረ-ነገር ምርመራ ውጤት የሚያመለክተው ለገበያ በሚቀርበው ወተት ምርት ላይ ሰፊ የጥራት መጓደል መኖሩን ያሳያል። የላቦራቶሪ ፍተሻ ከተደረገላቸው 264 የጥሬ ወተት ናሙናዎች መካከል 127ቱ (48.1%) የቅባት መጠናቸው ከተቀመጠው ስታንዳርድ በታች ሆኖ ተገኝቷል፤ ይህም ወተቱ በቂ የአልሚ ምግብ ይዘት የሌለው መሆኑን ያረጋግጣል። በተጨማሪም 53 (20.1%) የጥሬ ወተት ናሙናዎች የቅዝቃዜ ልኬት (Freezing Point) መስፈርቱን ሳያሟሉ ቀርተዋል፤ ይህም በምርት አቅርቦት

ሰንሰለቱ ላይ ወተት በውኃ የመበረዝ (Water Adulteration) ወይም የጥራት ማጭበርበር ድርጊት በስፋት ሊኖር እንደሚችል በግልጽ ይጠቁማል።

**የወተት አፍላቶክሲን (Aflatoxin M1) ምርመራ አፈጻጸም**

የጥሬ ወተት አፍላቶክሲን ደህንነት ፍተሻ ሥራን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ 104 የጥሬ ወተት ናሙናዎች ላይ የአፍላቶክሲን የላቦራቶሪ ምርመራ የተከናወነ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ በ10 (9.6%) ናሙናዎች ላይ የታየው የብክለት መጠን ከተፈቀደው ከፍተኛ የደህንነት ደረጃ በላይ ሆኖ ተመዝግቧል። ከተፈቀደው ገደብ በላይ በጥሬ ወተት ውስጥ የተገኘው መርዛማ ንጥረ-ነገር የወተት ላሞች የተመገቡት መኖ በአፍላቶክሲን የተበከለ መሆኑን የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ፤ መርዙ በምግብ ሰንሰለት ወደ ሰው ተላልፎ ለከባድ የጤና ችግሮች (ጉበት ካንሰር) ስለሚዳርግ ጠንካራ የቁጥጥር ተግባራዊ ማድረግን ይሻል።

**የሥጋ እና ወተት ማይክሮባዮሎጂካል ጥራት ፍተሻ እና የበካይ ተህዋሲያን ምርመራ አፈጻጸም**

የባክቴሪያ ቆጠራ ከተደረገላቸው 133 የወተት ናሙናዎች ውስጥ እጅግ አሳሳቢ የሆነ የብክለት መጠን የተመዘገበ ሲሆን፤ 115 ናሙናዎች (86.5%) በኮሊፎርም (Coliform count) እና 86 ናሙናዎች (64.7%) በኮአጉሌዝ ፖዚቲቭ ስታፊሎኮከስ አውረስ (*Staphylococcus aureus*) ከመደበኛው መስፈርት በላይ በከፍተኛ ሁኔታ ተበክለው ተገኝተዋል። ይህም በሀገሪቱ የወተት አቅርቦት ሰንሰለት ላይ ሰፊ የንጽህና ጉድለት መኖሩን ያረጋግጣል። በተጨማሪም በ 4ኛ ሩብ አመት ውስጥ በምርት ጥራት ችግር ተጠርጥረው ከተመረመሩት 10 የዶሮ ሥጋ እና 1 የዓሳ የናሙናዎች መካከል ግማሽ ያህሉ ማለትም 5 ናሙናዎች በሳልሞኔላ (Salmonella) በሽታ አምጭ ባክቴሪያ የተበከሉ ሆነው የተገኙ ሲሆን፣ ከእነዚህም ውስጥ አንድ ናሙና በተጨማሪ በሊስተሪያ ሞኖሳይቶጂነስ (*Listeria monocytogenes*) አደገኛ ባክቴሪያ የተበከለ መሆኑ ተረጋግጧል። እነዚህ ግኝቶች በምግብ አቅርቦት ሰንሰለቱ ላይ ከፍተኛ የደህንነት ስጋት መኖሩን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

- **የፀረ-ተህዋሲያን መድኃኒት መላመድ (AMR/AST) የላቦራቶሪ ፍተሻ አፈጻጸም**

የፀረ-ተህዋሲያን መድኃኒት መላመድ ምርመራ ለማካሄድ በበጀት ዓመቱ ውስጥ 80 ታቅዶ **147 በሽታ አምጪ ባክቴሪያዎችን** (183.8%) በመለየት በቫይቴክ አውቶሜትድ ማሽን እና በዲስክ ዲፊውዥን ዘዴዎች ፍተሻ ተከናውኗል። የተለዩት ባክቴሪያዎች 108 ኢኮላይ፣ 3 ሳልሞኔላ እና 36 ስታፊሎኮከስ አውረስ ናቸው። የላቦራቶሪ ምርመራ እንደሚያሳው የጀርሞች መድኃኒት የመቋቋም አቅም እጅግ አደገኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። በተለይም ኢኮላይ (*E. coli*) ለአምፕሲሊን 97.2% እና ለስትሬፕቶማይሲን 56.4% መላመድ ያሳየ ሲሆን፤ ስታፊሎኮከስ አውረስ ደግሞ ለፔኒሲሊን 100% ሙሉ በሙሉ እና ለቴትራሳይክሊን 66.7% ከፍተኛ የመድኃኒት መቋቋም ችግር አስመዝግቧል።

- **ማጠቃለያ እና የሬጉላቶሪ ምክረ-ሐሳብ:-** በጥሬ ወተት ላይ የተገኘው ከፍተኛ የጥራት ጉድለት (በውኃ መበረዝ)፣ የአፍላቶክሲን ብክለት፣ በሥጋና ወተት ምርቶች ላይ የታዩት እንደ ሳልሞኔላ እና ሊስተሪያ ያሉ አደገኛ ተላላፊ ተህዋሲያን ብክለት፣ እንዲሁም በላቦራቶሪ የተረጋገጠው የፀረ-ተህዋሲያን መድኃኒት መላመድ (AMR) ችግር አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የሕዝብ ጤና እና የደህንነት ስጋት መሆናቸውን ያሳያል። ስለሆነም ይህንን አሳሳቢ አደጋ ለመግታት በእንስሳት ምርት አያያዝ፣ በቄራዎችና እርባታ ቦታዎች የንጽህና ቁጥጥር ሥርዓት (Sanitation & Hygiene) ላይ ጥብቅ ቁጥጥር መዘርጋት ይገባል፤ በተጨማሪም አርቢዎችና የእንስሳት ሕክምና ባለሙያዎች የመድኃኒት አጠቃቀም መመሪያዎችን በአግባቡ እንዲተገብሩና ያለ ሐኪም ትዕዛዝ የሚደረገውን የተሳሳተ የመድኃኒት አቅርቦትና አጠቃቀም (Antimicrobial Stewardship) በስፋትና በትኩረት ለመቆጣጠር የሚያስችል አስገዳጅ የሬጉላቶሪ ሥርዓት መተግበር አለበት።
- በበጀት አመቱ  ደህንነቱና ጥራቱ ተረጋግጦ ወደ ተቀባይ አገራት ለሚላክ ስጋና ተረፈ ስጋ የተሰጠ የደህንነትና ጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለምርቶቹ የተሰጠ የደህንነትና ጤንነት ማረጋገጫ ሰረተፊኬት በዓመቱ 9,000 ለማከናወን ታቅዶ7,669 ተከናውኗል፡ የእቅዱ አፈፃፀም 85.2 % ነው

## የተለያዩ በቅንጅት የተፈፀሙ ተግባራት

- የስጋ እና የተረፈ ስጋ ኤክስፖረቱን ለማሳደግ ከባለድርሻ አካላት ማለትም ከኤርፖርት ካርጎ፣ ከጎምሩክ ኮሚሽን፣ ከብሔራዊ ደህንነት፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከብሔራዊ ባንክ፣ ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ከወተት

እምራቶች፣ ከዶሮ አረቢ ማህበር፣ ከስጋ አምራች እና ላኪዎች ማህበር፣ ከሁሉም ኤክስፖርት ቄራዎች እና ከቄራ ስርቢስ ተጠቃሚዎች ከድራይቭ ፕሮጅቶት ባገኘነው የገንዘብ ድጋፍ  ከሬጉላቶሪ አኳያ ባሉ መልካም አጋጣሚዎች እና ተግዳሮቶች ዙሪያ ውይይት ተርግጓል፡፡

- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የእንስሳት ምርት ሬጉላቶሪ ዘርፍ ላሉ ስጋ ምርመራና ሰረተፊኬሺን ባለሙያዎች የንድፈ ሃሳብ እና ተግባራዊ ስልጠና በስራ ክፍሉ ከፍተኛ ባለሙያዎች ተሰጥቷል፡፡
- በኤክስፖርት ቄራዎች ላይ የሚታዩትን የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ችግሮች ለማስተካከል እንዲቻል ለሁሉም ኤክስፖርት ቄራ ተወካዮች በድራይቭ ፕሮጀክት ድጋፍ የንድፈ ሃሳብና የተግባር ስልተና ተሰጥቷል፡፡
- የስጋ ሴክተሩን ዲጅታላዝ ለማድረግ ሲሰተሙ አልቆ ለባለሞያዎች ስልጠና ተሰጥቶ ወደ (በሰርቢስ ዲጅታላይዜሽን፣ኢ-ለርኒግ እና ዌብሳይት) ተግባር እንዲገባ ተደርጓል፡፡
- በኮሜርሻል ዶሮ እርባታ ላይ የተሰማረቱን አምራቾች መልካም የአመራረት ሥርዓት (GMP,GHP) አተገባበር ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በድጋፍና ክትትል በመለየት የማስተ ካከያ እርምት አካሄደው ወደ ምዝገባና ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማውጣት ሂደት እንዲገቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ተሰርቷል፡፡
- የኦዲት ኢንስፔክሽን ግኝት መሰረት በማድረግ የዶሮ ቄራ አቋቁመው በመስራት ላይ የሚገኙ አምራቾች በመስክ ደጋፍና ክትትል ችግሮችን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ እንዲያካሄዱ  ውይይት በማካሄድ አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡
- በ1 የዶሮ ቄራ ተሰጣቸውን የኦዲት-ኢንስፔክሺን ግኝት ላይ የማስካከያ እርምጃ በመውሰድ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲውስድ ተደርጓል፡፡
- ከSNV Bridge+ ፕሮጆክት እና ከUNIDO ፕሮጀክት ጋር በመተባባር የእንሰሳት ውጤት ጥራትና ደህንነት ረቂቅ ደንብ ላይ 70 ባለ ድርሻ አካላት የተሳተፉበት  የማስተቸት እና የማስተዋወቅን ስራ ተከናውኗል፡፡
- በሪስቶር ፕሮጀክት ጋር በመተባበር የእንስሳት ውጤት ጥራትና ደህንነት ረቂቅ ደንብ ላይ 50 ባለ ድርሻ አካላት የተሳተፉበት ሁለተኛ ዙር የማስተቸት፣ ግብዓት የማሰባሰብ እና የማስተዋወቅ ስራ ተከናውኗል፡፡
- ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ከእንስሳት ምርት ጥራት፣ጤንነት እና ደህንነት ጋር የተያያዙ 4 ነባር ስታንዳርዶች የመከለስ ስራ ተሰርቷል፡፡

- በኤፍ ስ አር ፕሮጀክት ድጋፍ ክለሳ የተደረገባቸውን 4 ናሺናል እስታንዳርዶች ለባለ ድርሻ አካላት የማስተቸት ስራ ተከናውኗል፡፡
- የእንስሳት ምርትና ማምረቻ ተቋማት ምዝገባ ለማካሄድና የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል የፈቃድ እና ምዝገባ መመሪያ draft ተዘጋጅቷል፡፡
- የእንሰሳት ምርት ጥራት፣ጤንነትና ደህንነት የሬጉላቶሪ ስራዎችን የሚያግዙ መመሪያዎች በሁሉም የምርት አይነቶች የመጀመሪያ ድራፍት ማዘጋጀት ሂደት ወደ ማጠናቀቅ ይገኛል፤
- ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን በጋራ በእንስሳት ምርት ጥራት፣ጤንነትና ደህንነት ላይ ለሚሰሩ 65 ኢንስፔክተሮችና ሰርተፊኬሽን ባለሙያዎች የዓቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ከኦሮሚያ የግብርና ግብአቶችና ምርት ቁጥጥር ባለስልጣን ጋር በመተባበር ለ60 ባለሙያዎችና የወተት አመራች ህብረት ስራ ተወካዮች በእንስሳት ምርት ጥራት ኢንስቴክሽን እና በሬጉላቶሪ ዙሪያ ያሉትን የህግ ማእቀፎች ለሁለት ቀናት ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ከSNV Bridge+ ፕሮጆክት በተገኘ የትብብር ድጋፍ የጥሬ ወተት ደህንነት እና ጥራት ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡
- ከSNV Bridge+ ፕሮጆክት በተገኘ የትብብር ድጋፍ ለጥሬ ወተት ትራንስፖርቴሺን፣ ለመሰብሰቢያ ቦታዎች እና ለማቀዝቀዣ ማዕከላት ላይ የወተት ንፅህና እና ደህንነት አጠባበቅ ጋይድላይን እና ለኮመሪሻል የወተት ላም እርባታ ላይ የጥሬ ወተት ንፅህና እና ደህንነት አጠባበቅ ጋይድላይን ዜሮ ረቂቅ ተዘጋጅቷል፤
- ከSNV Bridge+ ፕሮጆክት በተገኘ የትብብር ድጋፍ በጥሬ ወተት አመራረት፣ ጥሬ ወተት መሰብሰቢያ ማዕከል፣ በመሸጫ ገበያ፣ ንጽህና አጠባበቅ ዙሪያ እሴት ሰንሰለቱን ተከትሎ በዘርፉ ለተሰማሩ ለ2050 ተሳታፊዎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ተከኗውኗል፤

3.2 በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች

- በአጠቃላይ በበጀት አመቱ በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ ወደ ውጭ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ለ650,000 ወደ ውጭ የሚላክ የቁም እንሰሳት/ዳልጋ ከብት፣ ግመል/ በግ፣ ፍየል/ በኳራንትን ጣቢያዎች ውስጥ በማቆየት አስፈላጊን ክትባትና የጤና ምርመራ በማድና ጥራቱና ጤንነቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 676,321 (100+%) የቁም እንሰሳት ጥራትና ጤንነቱን በማረጋገጥ ወደ ተቀባይ ሀገራት መላክ ተችሏል፡፡
- በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ጥራቱ፣ ደህንነቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የሚላክ 573000 የአንድ ቀን ጫጩት እና የለማ እንቁላል ኤክስፖርት ለማድረግ ታቅዶ 442059 የሳኒተሪ ሰርተፍኬት በመስጠት ወደ ውጭ ሀገር እንዲላክ ተደርጓል፡፡ ይህም ከእቅዱ አንጻር 77% አፈጻጸም ፡፡የታቀደው ኤክስፖርት መጠን የወረደበት ምክንያት የገበያ ፍላጎት በማጣቱ ሳይሆን፣ በሀገር ውስጥ የሚታየውን ከፍተኛ ፍላጎት ለማሟላትና የሀገር ውስጥ ገበያን ለማረጋጋት ሲባል በግብርና ሚኒስቴር እና በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ውሳኔ ወደ ውጭ የመላክ እቀባ በመጣሉ ነው፡፡
- በበጀት አመቱ ወደ ተቀባይ ሀገራት የማርና ሰም ምርት ለሚል ድርጅቶች የኢንስፔክሽን እንዲሁም የላብራቶሪ ምርመራ ተደርጐላቸው ለ200 ቶን ማርና ሰም ለመላክ ታቅዶ 190.563 ቶን (90%) የጤና አገልግሎት ሰርትፊኬሽን በመስጠት እንዲላኩ ተደርጓል፡፡
- በበጀት አመቱ ለ4,500,000 ያለቀለት ቆዳና ሌጦ የቨተርነሪ ሳኒተሪ ሰተፍኬት ለመስጠት ታቅዶ 5,138,971 100%) የሳኒተሪ ሰርትፊኬት በመስጠት ከሀገር እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸም 100% ነዉ
- በዚህ 9 ወር ዉስጥ ለ738,492 ወደ ሀገር የሚገባ የአንድ ቀን ጫጩትና የለማ እንቁላል ጤንነቱ እና ደህንነቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 2,650,681 (100+%) ተከናውኗል አፈጻጸም ከፍተኛ መሆን ዋነኛው ምክንያት "የለማት ትሩፋት" አገራዊ መርሃ-ግብር በዘርፉ ላይ የፈጠረው ከፍተኛ መነቃቃትና በሀገር ውስጥ የታየው ሰፊ የዶሮ እርባታ ፍላጎት ነው፡፡
- በበጀት አመቱ ለ350 ወደ ሃገር ውስጥ የሚገባ የተሻሻለ ዳልጋ ከብት ጤንነቱ እና ደህንነቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 793 (100+%) ተከናውኗል ይህ ከፍተኛ ስኬት በሀገር ውስጥ ያለውን የወተት ምርታማነት ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ ሲሆን፣

ተቋሙም አስፈላጊውን የጤና ምርመራና የኳራንቲን ቁጥጥር በማድረግ ምርጥ ዝርያ ያላቸው ከብቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ አመቻችቷ።

- በበጀት አመቱ 160,000 ወደ ዐገር ለሚገባ አባላዘር ጤንነቱ እና ደህንነቱ የማረጋገጥ ሥራ ለመስራት ታቅዶ 148359 (93%) ተከናውኗል።
- በበጀት አመቱ ለቁም እንስሳት፣ ለእንስሳት ምርቶች እና ለተረፈ ምርቶች ኤክስፖርት ዘርፍ በተሰማሩ70 ድርጅቶች ላይ የኢንስፔክሽን ሥራ ለማከናወን ታቅዶ፣ በ 81 ተቋማት ላይ የቁጥጥር ሥራው ተፈጽሟል። ይህም ከዕቅዱ አንጻር >100% አፈጻጸም ያስመዘገበ ሲሆን፣ በተቋማቱ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት የጥራትና የሬጉላቶሪ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ የውጭ ንግድ ሂደቱ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን አስችሏል።
- በበጀት አመቱ ከውጭ ለሚገቡ የእንስሳት ግብዓቶች (የአንድ ቀን ጫጩት፣ የዘር ፈሳሽ፣ የለማ እንቁላልና ጊደሮች) የጤናና የጥራት ደረጃን ለማረጋገጥ ለ4000 ናሙናዎችን ለማስመርመር ታቅዶ 3894 ናሙናዎች እንዲመረመሩ ተደርጓል። አፈጻጸም 97% ነዉ ።ስራው ከእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ጋር በቅንጅት የተከናወነ ሲሆን፣ ይህም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ግብዓቶች ከማንኛውም በሽታ ነፃ መሆናቸውንና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ታስቦ የተከናወነ ቁልፍ የጥራት ቁጥጥር ተግባር ነው።
- በበጀት አመቱ በተቀባይ ሀገራት መስፈርት መሠረት ለኤክስፖርት ለተዘጋጁ 160,000 የቁም እንስሳት የደም ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ፣ ለ156,345 እንስሳት ምርመራው ተከናውኗል። አፈጻጸም>100% በማሳካት የላቀ የታየበት ተግባር ነው። በምርመራው ውጤት መሠረት የጤና ችግር የተገኘባቸው 13,234 እንስሳት ወደ ውጭ እንዳይላኩ ተለይተው የተቀነሱ ሲሆን፣ ይህም በተቀባይ ሀገራት ላይ ሊከሰት ይችል የነበረውን የጤና ስጋትና በሀገሪቱ የውጭ ንግድ ላይ ሊፈጠር ይችል የነበረውን እገዳና መስተጓጎል አስቀድሞ ለመከላከል አስችሏል።

3.3 የእንስሳት መድኃኒት ጥራት፣ ደህንነትና ፈዋሽነትን ማረጋገጥ

- የእንሰሳት መድሃኒት ጥራት ደህነነትና ፈዋሽነነት ማረጋገጥ ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ የእንስሳት መድሃኒት በአጠቃላይ በበጀት አመቱ 3500 ቶን ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ

ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ የእንስሳት መድሃኒት ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ታቅዶ 3916.63 ቶን (100+%) የእንስሳት መድኃኒት ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል:: አፈጻጸሙም ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ተገልጋዮች አገልግሎቱን ፈልገው በብዛት ባመምጣታቸው ነው::

- በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ተገምግሞ፣ በኢንስፔክሽን ስርዓትና በላቦራቶሪ ምርመራ ተረጋግጦ 120 የእንስሳት መድሃኒት ለመመዝገብ ታቅዶ 132(100+%) የእንስሳት መድኃኒት እንዲመዘገብ ተደርጓል:: አፈጻጸሙም ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት አሰራሩ ዲጂታላይዝድ ከሆነ በኃላ አምራች ድርጅቶች ከሀገር ውስጥ ካለ ተወካይ በተጨማሪ የምዝገባ ሂደቱን የሚከታተሉት በመሆኑ የተለያዩ የመድሃኒት አማራጮች የመመዝገብ እድል በመፈጠሩ ነው፡
- በመድኃኒት ፊዚኮ-ኬሚካል ጥራትና ደህንነት ምርመራ አገልግሎት ዘርፍ፤ በ4ኛው ሩብ ዓመት በ90 ናሙናዎች ላይ ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ በ42 (46.7%) ናሙናዎች ላይ ፍተሻ የተካሄደ ሲሆን፣ በዓመቱ በአጠቃላይ 380 ናሙናዎችን ለመመርመር ታቅዶ 427 (108.2%) ናሙናዎችን ማስተናገድ ተችሏል:: ምርመራ ከተደረገላቸው ናሙናዎች ውስጥ 30 (7.3%) የሚሆኑት የጥራት መስፈርቱን ባለማሟላታቸው፣ ተገቢው አስተዳደራዊ እና የቁጥጥር (ሬጉላቶሪ) እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለመድኃኒት ሬጉላቶሪ ሥራ ክፍል ሪፖርት ተደርጓል::
- በመድኃኒት ማይክሮባዮሎጂ ጥራትና ደህንነት ምርመራ አገልግሎት፤ በሩብ ዓመቱ በ30 ናሙናዎች ላይ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ የ15 (50%) ናሙናዎች ፍተሻ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ዓመታዊ አፈጻጸሙ ደግሞ ከታቀደው 120 ናሙናዎች በላይ በመሆን 141 (117.5%) ናሙናዎች ላይ የማይክሮባዮሎጂካል ጥራት ምርመራ ተከናውኗል:: ከእነዚህም ውስጥ 1 (አንድ) ናሙና የማይክሮብያል ሊሚት ምርመራ መስፈርትን ሳያሟላ በመገኘቱ ተገቢው የሬጉላቶሪ እርምጃ እንዲወሰድበት ተደርጓል
- በመጨረሻም፣ በክትባት ጥራትና ደህንነት ምርመራ በኩል በሩብ ዓመቱ 5 ናሙናዎችን ለመመርመር ታቅዶ 9 የተከናወነ ሲሆን፣ ቀሪ 16 የክትባት ናሙናዎች ደግሞ ወደ አፍሪካ ኅብረት የክትባት ቁጥጥር ማዕከል (PANVAC) ተልከው በአሁኑ ወቅት ውጤታቸው በመጠባበቅ ላይ ይገኛል:: በዓመቱ በአጠቃላይ 20 ለመመርመር ታቅዶ በ16 (80%) የክትባት ናሙናዎች ላይ ምርመራ ተካሂዶ ውጤቱ ለሬጉላቶሪው ክፍል

የተላለፈ ሲሆን፣ እስካሁን ምርመራ የተደረገላቸው ሁሉም የክትባት ናሙናዎች ተፈላጊውን የጥራትና ደህንነት መስፈርት ሙሉ በሙሉ ማሟላታቸው ተረጋግጧል፡፡

➢ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት ለ410 የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ታቅዶ 351(85.6) ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰቷል፡፡

➢ የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን 682 የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን እናረጋለን ብለን አቅደን 550 (80.6%) የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን አካሂደናል፡፡

**በኢንስፔክሽን ወቅት ክፍተት የተገኘባቸውን ድርጅቶች ከታች የተዘረዘሩትን ተመጣጣኝ አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶባቸዋል፡፡**

- 3 (1 አስመጪ እና 2 ጅምላ አከፋፋይ) ድርጅቶችን የሶስት ወር እገዳ፣ 9 ድርጅቶች (2 አስመጪ እና 7 ጅምላ አከፋፋይ) የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ 10 ድርጅቶችን (3 አስመጪ እና 7 ጅምላ አከፋፋይ) የቃል ማስጠንቀቂያ እና (22 አስመጪ እና 23 ጅምላ አከፋፋይ) በኢንስፔክሽን ወቅት ክፍተት፣ በሰዓቱ ባለማሳደሱ እና በራሳቸው ፈቃድ ተሰርዟል፡፡

ሰንጠረዥ 1፡የኮንሳይንመንት ናሙና ተወስዶ ከደረጃ በታች በመሆናቸው እንዲወገዱ ወይም ወደ መጡበት ሀገር እንዲመለሱ የተደረጉ እና በመደረግ ላይ ያሉ መድኃኒቶች በብዛት እና ዋጋ

| SN | Generic Name | Dosage form | Unit | Quantity | Total cost (ETB) | ያለበት ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Oxytetracycline 10 % (1 bach) | Injection | Vial | 2150 | 191,743.20 | ተወግዷል |
| 2 | Oxytetracycline 20 % 5gm (3 bach) | Powder | sachet | 24756 | 1,252,653.00 | ተወግዷል |
| 3 | Oxytetracycline 20 % 100 gm( 1 bach) | Powder | Sachet | 984 | 470,155.20 | ተወግዷል |
| 4 | Oxytetracycline 20 % (1 bach) | Powder | sachet | 10000 | 1,234,115.00 | ተወግዷል |

| SN | Generic Name | Dosage form | Unit | Quantity | Total cost (ETB) | ያለበት ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | Oxytetracycline 20 % (2 bach) | Powder | sachet | 189000 | 2,176,413.53 | ኳራንቲን ተደርጓል |
| 6 | Oxytetracycline 20 % (1 bach) | Powder | Vial | 84800 | 6,963,002.45 | ተወግዷል |
| 7 | Enroflocaciline | Injection | Vial | 744 | 121,478.44 | ተወግዷል |
| 8 | Toltrazuril (2.5%) | Injection | Vial | 1383 | 424,683.24 | ተወግዷል |
| 9 | Tetramisole oxyclosanide 3400 (5 bach) | Bolus | Box | 1753 | 1,363,693.76 | ኳራንቲን ተደርጓል |
| 10 | Ivermectine (1 bach) | Injection | Vial | 160000 | 3,827,439.36 | ወደመጣበት ሀገር ተመልሷል |
| 11 | Oxytetracycline 10 % (1 bach) | Injection | Vial | 20800 | 1289044.016 | ተወግዷል |
| 12 | Ivermectine (2 bach) | Injection | Vial | 42,500 | 2,610,241.37 | ተወግዷል |
| 13 | Ivermectine (2 bach) | Injection | Vial | PMS (0) | በገበያ የተገኘ የለም | |
| 14 | Ivermectine (1 bach) | Injection | Vial | PMS (1880 vial) | Quarantine | ኳራንቲን ተደርጓል |
| 15 | Flucazash sheep | Bolus | Box | 1050 boxes | Quarantine | |
| | **sub total** | | | | **21,924,662.55** | |

- ✓ የመጠቀሚያ ጊዜው በማለፉ 50 ካረቶን AMONTONG 5% እንዲወገድ ተደረጓል፡፡
- ✓ የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፉ እና የተሰበረ 143 ካረቶን oxy 10% እንዲወገድ ተደረጓል፡፡

በእንስሳት መድሃኒት ሬጉላቶሪ ስር ያሉ አገልግሎቶችን በ ድህረ ገጽ እንዲከናወኑ (ዲጂታላይዝድ) ማድረግ

- ➢ በአጠቃላይ በጀት ዓመት 6 በእንስሳት መድሃኒት ሬጉላቶሪ ስር ያሉ አገልግሎቶችን በ ድህረ ገጽ በኢሰርቪስ እየተከናወኑ ሲሆን ወደ 15 የሚደረሱ አገልግሎቶች በ መሶብ ማዕከል እንዲሰጡ ተደርጓል ሌሎች 10 አገልግሎቶች በ መሶብ ማዕከል እንዲሰጡ

ሙሉ ዝግጅት የተደረገ ሲሆን ወደ የተቀሩት 4 አገልግሎቶች በዋና መስሪያቤት ኢስረቪስ እንዲገቡ በዝግጅት ላይ እንገኛለን፡፡ አፈጻጸሙም 100% ሆኗል፡፡

3.4 ጥራትና ደህንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ

1. **የአበይት ተግባራት አፈጻጸም**

**1.1.** ለመኖ ንግድ ተቋማትና ባለሙያዎች፣ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫና ሰርተፊኬሽን፤ በበጀት ዓመቱ በ565 ተቋማትና ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ560 (99.1%) ተቋማትና ባለሙያዎች ተሰጥቷል፡፡

- በዚህ በጀት ዓመት የ197 የመኖ ንግድ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት ለማድረግ ታቅዶ ለ146 የመኖ ንግድ ድርጅቶች እድሳት የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 74.11% ሆኗል፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነው ተቋማት ባለመቅረባቸው ነው፡፡

- በዚህ በጀት ዓመት 64 አዲስ እና ምትክ የብቃት ማረጋግጫ ለመሰጠት ታቅዶ 86 አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እና 29 ምትክ፣ በድምሩ 115 የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ ›100% ሆኗል፡፡

- በዚህ በጀት ዓመት የ239 የእንስሳት መኖ ባለሙያዎችን የብቃት ማረጋገጫ ዕድሳት ለማከናወን ታቅዶ 161 ሲከናወን፣ አፈጻጸሙ 67.36% ነው፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነው ዕድሳት ባልተካሄደባቸው ተቋማት የሚሰሩ ባለሙያዎች ባለመቅረባቸው ነው፡፡

- በዚህ በጀት ዓመት በመኖ ንግድ ተቋማት ለሚሰሩ 65 አዲሰና ምትክ የመኖ ባለሙያዎች ምዝገባና የሙያ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ፣ 110 አዲስ እና 28 ምትክ በድምሩ 138 የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ ›100% ሆኗል፡፡ አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነው በርካታ ባለሙያዎች በመልቀቃቸው ምክንያት አዳዲስ ባለሙያዎች በመቀጠራቸው ነው፡ :

1.2. በዚህ በጀት ዓመት በኦንላይን በኤሌክትሮኒክስ ሲንግል ዊንዶው ለመኖና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አስመጪዎች ለ <u>7000</u> ቶን የግዥና የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ <u>11337.035</u> ቶን የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ ከ100% ሆኗል፡፡

አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነው አዲስ አስመጪዎች ቁጥር በመጨመራቸውና ጥያቄው በብዛት በመቅረቡ ነው፡፡

- በዚህ በጀት ዓመት ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ 6000 የመኖ ግብዓት በኦንላይን ሲንገል ዊንዶው የመልቀቂያ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ፣ ከምርቱ ጋር የሚቀርበውን የጥራት ማረጋገጫ ሰነዶችንና በመኖ ኢንስፔክተሮች የፊዚካል ኢንስፔክሽን በማካሄድ **ለ7263.219** ቶን የመልቀቂያ ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን፣ አፈጻጸሙ 46.67 % ነው፡፡ በተሰጠው የግዢና የማስገቢያ ፈቃድ መጠን ስላልቀረበ ነው፡፡

- አዳዲስ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር የሰነድ ግምገማ በማካሄድ በዚህ በጀት ዓመት 100 የምርት ዓይነቶችን ለመመዝገብና ወደ አገር እንዲገባ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ በአስመጪዎች የ171 ምርት ጥያቄ ቀርቦ በተደረገው የሰነድ ማጣራት 10 የምርት ዓይነት መስፈርቱን ስላላሟላ ሲወድቅ፣ 130 ምርት ተመዝግቦ ጊዜያዊ የምዝገባ ሰርተፊኬት ተሰጥቷል፣ ቀሪ 31 ምርት በሰነድ ማጣራ ሂደት ላይ ነው፡፡

- ለወጪ ንግድ ለሚቀርብ የእንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ በዚህ በጀት ዓመት 300 የቅድመ ማስወጫ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ የተቀባይ ሀገራትን መስፈርት ላሟላ 442 የቅድመ ማስወጫ ሰርተፊኬት የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ሆኗል፡፡ በዚህ የመኖ ወጪ ንግድ የቅድመ ማስወጫና በጣቢያዎች የመልቀቂያ ፈቃድ ተሰጥቶ 86,091.85 ቶን የመኖ ጥሬ ዕቃ ወደ ተለያየ ሀገራት የተላከ ሲሆን ከዚህ ወጪ ንግድ 42,311,877 የአሜሪካ ዶላር ለሀገር ማስገኘት ተችሏል፡፡

## 1.3. በእንስሳት መኖ እና ተቋማት ኢንስፔክሽን ማካሄድ፤

**በበጀት ዓመቱ** በ384 ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ታቅዶ በ412 (›100%) ተቋማት ላይ የኢንሰፔክሽን ስራዎችን ለማከናወን ተችሏል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

- በዚህ በጀት ዓመት 100 ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን በመኖና የመኖ ግብዓት አስመጪ ተቋማት ለማካሄድ ታቅዶ 105 (›100%) እንዲሁም ለቅድም ፈቃድ በ6 ተቋማት በድምሩ 111 ኢንስፔክሽን ተፈጽሟል፡፡
- በዚህ በጀት ዓመት በመኖ አከፋፋይ ተቋማት 8 ድህረ-ፈቃድ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ታቅዶ 4 የተከናወነ ሲሆነ አፈጻጸሙ 50% ነው፡፡
- በዚህ በጀት ዓመት በእንስሳት መኖ ጥሬ እቃ አምራች ተቋማት 40 ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ታቅዶ 30 (75%) የተፈጸመ ሲሆን፣ በ7 ተቋማት ቅድመ-ፈቃድ ኢንስፔክሽን ተከናውኗል፡፡ በድምሩ 37 ኢንስፔክሽን ተከናውኖ አፈጻጸሙ 92.5% ሆኗል፡፡
- በዚህ በጀት ዓመት በመኖ አምራች ተቋማት 132 ድህረ-ፈቃድ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ታቅዶ 136 (›100%) በላይ የተከናወነ ሲሆን፣ በተጨማሪም በቅድመ ፈቃድ ኢንስክሽን 10 ሲከናወን፣ በድምሩ 146 (›100%) በላይ ተከናውኗል፡፡
- በዚህ በጀት ዓመት በመኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ላኪ ድርጅቶች 104 ድህረ-ፈቃድ ኢንስፔክሽን ለማካሄድ ታቅዶ 104(100%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በቅድመ- ፈቃድ ኢንስፔክሽን 10 ተከናውኗል፡፡ በአጠቃላይ 114 (›100%) በላይ ተከናውኗል፡፡
- በዚህ በጀት ዓመት 25 የመኖ ግብአት አምራች ድርጅቶችን ወደ ሕጋዊ አሰራር ለማስገባት ታቅዶ፣ 30(100 %) ተቋማት ላይ ከህግ ባለሙያዎች ጋር በቅንጅት ክትትል በማድረግ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ እስካሁን 6 ድርጅቶች የብቃት ማረጋጫ ምስክር ወረቀት ለማውጣት ያመለከቱ ሲሆን 4 የዱቄት ተረፈ-ምርት አምራች ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወስደዋል፡፡
- ከመኖ ጥራትና ደህንነት አኳያ ከህዝብ ለሚቀርብ 8 ጥቆማ ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ 2 ሲከናወን አፈጻጸሙ 25 % ሆኗል፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅ ሊል የቻለው የቀረበ ጥቆማ ባለመኖሩ ነው፡፡
- በዚህ በጀት ዓመት 160 የተቀነባበረ መኖ ናሙና ለጥራት ምርመራ ለማሰባሰብ ታቅዶ 251(>100%) የተከናወነ ሲሆን፣ ሲሆን አፈጻጸሙ በጣም ከፍተኛ ሊሆን የቻለው ለስራው በቂ የበጀት ድጋፍ ከኤስ ኤን ቪ ፕሮጀክት በመገኘቱ እና ከመንግስት ተቋም የገአልግሎት ጥያቄ በመቅረቡ ነው፡፡

**በኢንስፔክሽን ግኝት ላይ የተወሰደ እርምጃ፡-**

- በአንድ የእንስሳት መኖ አስመጪ ድርጅት እስከሚወገድ ድረስ ተለይቶ እንዲቀመጥ ተደርጎ የነበረ የመኖ ግብአት የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት እንዲወገድ ተደርጓል፡፡ የተወገዱ ግብዓቶች፡-(Dololayit-------6300 sache,Resergen-----1997 sachet, Rminivt--321battle/100ml,Floxivet---------22 litter,Aminovit powder--------3 sachet
- በአስመጪዎች የ171 መኖ ምርት ለማስመዝገብ በቀረበ ጥያቄ በተደረገው የሰነድ ማጣራት 10 የምርት ዓይነት መስፈርቱን ስላላሟላ ውድቅ ተደርጓል፣
- ዓመታዊ ዕድሳት በወቅቱ ላልፈጸሙ 65 የመኖ ንግድ ተቋማት፣ የብቃት ማረጋጫ ምስክር ወረቀታቸው በመመሪያ መሠረት ከመሰረዙ በፊት እድሳት እንዲያከናውኑ በደብዳቤ እንዲያውቁት ተደርጓል፤
- የመጀመሪያ ደረጃ ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ለ 89 የመኖ ንግድ ተቋማት የተጻፈ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ፡-
  - ✓ 51 ድርጅቶች ከደረጃ በታች የሆነ መኖ አምርተው በገበያ ላይ በማዋላቸው ምክንያት፤
  - ✓ 38 ድርጅቶች በንጽህና ጉድለት፣ ባልተሟላ ባለሙያ ሲሰሩ በመገኘታቸው፣ ሳያስፈቅዱ የቦታ ለውጥ በማድረጋቸው፣ በኢንስፔክሽን ወቅት በአድራሻቸው በመገኘት መጋዘናቸውን ለኢንስፔክተሮች ባለማሳየታቸው በመሳሉት ምክንያቶች፣
- በመኖ ናሙና ምርመራ ውጤት መሰረት በናሙናው የሚወከለውን መኖ ከገበያ እንዲያሰባስቡ በደብዳቤ ከተጠየቁ 51 መኖ አምራች ድርጅቶች መካከል፡-
  - ✓ አንድ ድርጅት በገበያ ላይ ያሰራጨውን 10 ኩ/ል የጀማሪና 5ኩ/ል የቁብ መኖ አሰባስቧል፣
  - ✓ 5 ድርጅቶች ምርቱ በጥቅም ላይ ስለዋለ ማሰባሰብ እንዳልቻሉ በጽሁፍ አሳውቀዋል፡፡
  - ✓ 3 መኖ አምራች ድርጅቶ ቶክሲን ባይንደር (Toxin Binder) በሚያመርቱት መኖ ውስጥ የሚጨምሩና የውስጥ ጥራት ቁጥጥር SOP ያላቸው መሆኑን በክትትል ኢንስፔክሽን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡
  - ✓ ለ42 ድርጅቶች ቶክሲን ባይንደር ኢንዲጠቀሙ እና SOP እንዲያዘጋጁ በመስክ ግብረመልስ ተሰጥቷቸዋል፤

- **እገዳን በተመለከተ፡-** 2 ድርጅቶች የእገዳ ደብባቤ የተጻፈባቸው ሲሆን አንዱ የእንስሳት መኖ አምራች ተቋም የምርት እና ጥራት ቁጥጥር ባለሙያ እንደሌለው በመረጋገጡ፣ ሁለተኛው ድርጅት ደግሞ የቦታ ለውጥ ሲያደርግ ለባለስልጣኑ ባለማሳወቁ እና በኢንስፔክሽን ወቅት አድራሻ ቀይሮ በመገኘቱ ሲሆን፣ በመመሪያ ቁጥር 16/2010 አንቀጽ 29 የተጠቀሰውን ድንጋጌ የጣሰ በመሆኑ፣ ተቋሙ ጉድለቱን እስኪያሟላ ድረስ እንዲታገድ ተደርጓል፣
- **እገዳ ማንሳትን በሚመለከት፡-** የቦታ ለውጥ ሲያደርጉ ባለማሳወቃቸው፣ መረጃ ባለመስጠታቸው እና በተጓደለ ባለሙያ ሲሰሩ በመገኘታቸው የታገዱ 4 ተቋማት ጉድለታቸውን ማስተካከላቸውን ባቀረቡት ደብዳቤ እና በኢንስፔክሽን በመረጋገጡ የተጣለው ዕግድ ተነስቷላቸዋል፡፡
- **ስረዛን በሚመለከት** አንድ መኖ አምራች ድርጅት ባለሙያ በሌለበት (ምርት ጥራት ተቆጣጣሪ እና የምርት ክፍል ኃላፊ በሌሉበት) ማሽን ኦፕሬተሩ መኖ ሲያመርት በመገኘቱ የመጀመሪያ ደረጃ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ሳለ ማስጠንቀቂያውን በመተላፍ ሲሰራ በመገኘቱ የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ ተደርጓል፤

**1.4 የመኖ እና የመኖ ጥሬ ግብዓት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የጥራት እና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ**

- በበጀት ዓመቱ በ160 የመኖ እና የመኖ ጥሬ ግብዓት ናሙናዎች ላይ የጥራት እና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ በ251 ናሙናዎች ላይ ማከናወን የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም (›100%) ነው፡፡

## 3.5 ደረጃውን የጠበቀ የእንሰሳት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት የእንስሳት ውጤቶች ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ

የጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎት ደረጃ ማሳደግ

- የላቦራቶሪ አክሬዲቴሽን የክትትል ምዘና እና የተወሰዱ ማሻሻያዎች፡- የጥራት ምርመራ ማዕከሉ ዓለም አቀፍ የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ሥርዓትን አጠናክሮ በመተግበር ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ አክሬዲቴሽን አገልግሎት (EAS) ባደረገው ዓመታዊ የክትትል ምዘና (Assessment) በተለዩ የኦዲት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ ዕቅድ ተዘጋጅቶ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የማሻሻያ ሥራዎች ተጠናቀዋል፤ዝርዝር

አፈጻጸሙን የሚያሳዩ የሰነድ ማስረጃዎችና ሪፖርቶች ለዕውቅና ሰጪው ተቋም በወቅቱ ሪፖርት ተደርጓል፡፡

- የላቦራቶሪ ዕውቅና ሙሉ በሙሉ ማስቀጠል (Accreditation Maintenance)፡- የኢትዮጵያ አክሬዲቴሽን አገልግሎት ማዕከሉ ያከናወናቸውን የማሻሻያ ሥራዎች ውጤታማነት በጥብቅ መርምሮ ያረጋገጠ ሲሆን፤ በዚህም መሠረት ማዕከሉ ቀደም ሲል በፋርማሲዩቲካል፣ በኬሚካል እና በማይክሮባዮሎጂ ዘርፎች በ13 የላቦራቶሪ ምርመራ መመዘኛዎች አግኝቶት የነበረው ዓለም አቀፍ የሦስተኛ ወገን ዕውቅና ሙሉ በሙሉ እንዲቀጥል (Accreditation Maintenance) ኦፊሴላዊ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡ ይህም ማዕከሉ የሚሰጣቸው ደረጃቸውን የጠበቁ የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ አገልግሎቶች በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላቸውን ተዓማኒነትና ተወዳዳሪነት ይበልጥ የሚያጠናክር ስኬት ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አዳዲስ የምርመራ ዓይነቶች ላይ ተጨማሪ እውቅና ለማግኘትና ነባሩን አስጠብቆ ለማቆየት በርካታ ሥራዎች ታቅደው ተግባራዊ ተደርጓል፤ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- የጥራት አሰራር ሰነዶች (Documentation) ክላሳ፡ እስከዚህ 4ኛው ሩብ ዓመት ድረስ 18 የጥራት ማኔጅመንት መደበኛ የአሰራር ሰነዶችን (SOPs) ለመከለስ ታቅዶ፣ ከዕቅድ በላይ 22 ሰነዶችና አስፈላጊ ዶክመንቶች ተሻሽለውና ጸድቀው ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርገዋል፡፡
- የምርመራ ዘዴዎች ትክክለኛነት ማረጋገጫ (Validation/Verification)፡- በበጀት ዓመቱ በፋርማሲዩቲካል፣ በኬሚካል እና በማይክሮባዮሎጂካል ዘርፎች 10 የተለያዩ የምርመራ ዘዴዎችን ቫሊዴት/ቬሪፋይ ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሠረት ሙሉ በሙሉ (100%) ተግበራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት 10 ፕሮቶኮሎች (የምርመራ ስነ-ዘዴ መመሪያዎች) ጸድቀው ትግበራቸው ተጠናቆ ለሥራ ዝግጁ ሆነዋል፡፡
- የላቦራቶሪ መሣሪያዎች ልኬት ትክክለኛነት (Calibration & Traceability)፡- የላቦራቶሪ መሣሪያዎችን ዓለም አቀፍ የልኬት ትረሰብሊቲ (Metrological Traceability) ለማስጠበቅ የተከናወኑት ተግባራት የማዕከሉን የምርመራ ተዓማኒነት ከፍ አድርገውታል፡፡ እስከ በጀት ዓመቱ ማጠናቀቂያ ድረስ 200 ለመፈተሽ ታቅዶ 183 መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች (91.5%) የካሊብሬሽን እና የኮምፐሊያንስ ቬሪፊኬሽን

(Calibration & Compliance Verification) ሥራዎች ተከናውኖላቸዋል። ካሊብሬሽን ከተደረገላቸው መሣሪያዎች ውስጥ 178ቱ የተለያዩ የላቦራቶሪ ምርመራ ናሙና ማዘጋጃ ቮሉሜትሪክ ቁሳቁሶች ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ 5ቱ ከፍተኛ አናላይቲካል መሣሪያዎች (Advanced Analytical Instruments) ናቸው።

የላቦራቶሪ መሣሪያዎች ጥገና አፈጻጸም፡- በ4ኛው ሩብ ዓመት የቅድመ-ብልሽት መከላከልና 3 የፊዚኮ-ኬሚካል እና 1 የማይክሮባዮሎጂ በድምሩ 5 ወሳኝ መሣሪያዎች ላይ የተሳካ የማስተካከያ ጥገና ተከናውኗል። ዓመታዊ አፈጻጸሙን በተመለከተ 30 መሣሪያዎችን ለመጠገን ታቅዶ 16ቱ (53.3%) (5 የማይክሮባዮሎጂ እና 11 የፊዚኮ-ኬሚካል) ጥገና የተደረገላቸው ሲሆን፤ ለቀሩት 14 መሣሪያዎች በተባበሩት መንግሥታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት እና በግብርና ሚኒስቴር ዲራይቪ ፕሮጀክት ድጋፍ የጥገና አገልግሎት ግዥ ጨረታን በድጋሚ ለማውጣት በሂደት ላይ ይገኛል።

- አዳዲስ የላቦራቶሪ መሣሪያዎች ተከላ፡- የማዕከሉን የምርመራ አቅምና ዓይነት ሽፋን ለማሳደግ በበጀት ዓመቱ የተገዙ 3 አዳዲስ መሣሪያዎችን ተከላ በማከናወን ወደ ሥራ ለማስገባት በተያዘው ዕቅድ መሠረት፤ የ2 አዳዲስ መሣሪያዎች ተከላ የተከናወነ ሲሆን፣ በአንድ ነባር መሣሪያ ላይ ደግሞ ተጨማሪ የምርመራ አቅም ማሳደጊያ ቴክኖሎጂ እንዲገጠምለት ተደርጓል። እነዚህ መሣሪያዎች በግብርና ሚኒስቴር የዲራይቪ ፕሮጀክት ድጋፍ የተገዙ በመሆናቸው ማዕከሉ የሚሰጣቸውን የጥራት ቁጥጥር አገልግሎቶች በከፍተኛ ሁኔታ አሳድገዋል።
- ዓለም አቀፍ የላቦራቶሪዎች የብቃት ማረጋገጫ (PT) ተሳትፎ፡- የምርመራ ብቃትን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስመስከር በማዕከሉ ሥር የሚገኙ 5 ላቦራቶሪዎች በተለያዩ የፕሮፊሽንሲ (PT) መለኪያ ፍተሻዎች ላይ ተሳትፈዋል። በዚህም መሠረት በድራይቭ ፕሮጀክት ግዥ 19 የምርመራ ዓይነቶች፣ ከአሜሪካ ቴክሳስ ስቴት ኬሚስት ቢሮ በድጋፍ 2 የመኖ አፍላቶክሲን ናሙናዎች፣ እንዲሁም ከኤፍኤኦ ጋር በመተባበር ከእንግሊዝ አገር 1 የፀረ-ተህዋሲያን መድኃኒት መላመድ (AMR) ናሙና በድምሩ በ22 የምርመራ ዓይነቶች ላይ ፍተሻ ተካሂዷል። ከእነዚህም ውስጥ በ20 የምርመራ ዓይነቶች (90.9%) ላይ ከዓለም አቀፍ ደረጃ ጋር ተመሳሳይ የላቀ ውጤት በመመዝገቡ የማዕከሉ የምርመራ ትክክለኛነትና ተወዳዳሪነት ተረጋግጧል።

የተከናወነ የመኖ መረጃ እና አቅም ግንባታ ሥራዎች፡-

- በበጀት ዓመቱ ለ34 ወንድ እና 4 ሴቶች በድምሩ ለ38 ሰዎች በ GMP እና GHP ለመኖ ኢንስፔክተሮች፣ ላቦራቶሪ አናሊስቶችና የመኖ አምራች ተቋማት በኤስ ኤን ቪ ድጋፍ ስልጠና ተሰጥቷል።
- በበጀት ዓመቱ የተመዘገበ የመኖ ንግድ ተቋም፣ ባለሙያ፣ መኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መረጃዎችን 12 ጊዜ ለማደራጀት ታቅዶ የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 100% ነው።
- በኤስ.ኤን.ቪ. የበጀት ድጋፍ በ45 የመኖ ንግድ ተቋማት ላይ በተካሄድ የመልካም አመራረት (GMP) እና መልካም ንጽህና አጠባበቅ (GHP) አተገባር ላይ እና በመኖ ጥራትና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት ላይ ወንድ 69 ሴት 21 በድምሩ 90 ባለድርሻ አካላት በተገኙበት የምክክር መድረክ ተካሂዷል፤
- ከኤስ.ኤን.ቪ.. (SNV Ethiopia) በተገኘ የበጀት ድጋፍ በ2012 ዓ.ም. የተዘጋጀ 32 የመኖና የመኖ ግብዓት ደረጃ የመከለስ እና 10 አዳዲስ ደረጃዎችን፣ ከባለሥልጣኑ፣ ከመኖ ኢንዱስትሪ፣ ከምርምር ተቋም፣ ከዩኒቨርሲቲ እና ከኢትዮጵያ ስታንዳርድ ኢንስቲትዩት በተውጣጡ ባለሙያዎች ማዘጋጀት ተችሏል፤
- በተሻሽለው 32 የመኖና የመኖ ግብዓት ደረጃ እና 10 አዲስ በተዘጋጁ ደረጃዎች ላይ የባለድርሻ አካላትን አስተያየት ለመሰብሰብ የውይይት መድረክ የተዘጋጀ ሲሆን፣ በመድረኩ ላይ ከ40 የመኖ ንግድ ተቋማት፣ የኢትዮጵያ የመኖ ኢንዱስትሪ ማህበር፣ የእንስሳት ምርትና ግብዓት ጥራት ምርመራ ማዕከል፣ ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲቲዩት እና የመኖ ተቆጣጣሪዎች 50 ወንድ እና 15 ሴት በድምሩ 65 ሰው በተሳተፉበት ውይይት ተካሂዶ የማሻሻያ ሀሳብ የተሰባሰበ ሲሆን፣ በቀጣይ የሥራ ቡድኑ ከባለድርሻ አካላት በቀረበው አስተያየት መሰረት እንደገና ደረጃውን በማስተካከል ለTC፣ ከዚያም ለብሔራዊ ደረጃ አጽዳቂ የሚቀርብ ይሆናል።
- በዚህ በጀት ዓመት በእንስሳት መኖ ንግድ ስራ ዘርፍ ለመሰማራት መረጃዎችን ለመውሰድ ለቀረቡ 60 ተገልጋዮች ተገቢውን መረጃ ለመስጠት ታቅዶ ለ62 አገልግሎቱን ፈልገው ለሚመጡ ተገልጋዮች መረጃ የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው።
- በዚህ በጀት ዓመት ከ66 የመኖ ማምረቻ ተቋማት የምርት መረጃ ለማሰባሰብና ለማደራጀት ታቅዶ ከ 50 ድርጅቶች መረጃ ተሰባስቧል። አፈጻጸሙ 53% ነው።

- ማዕከሉ በበጀት ዓመቱ የአመራርና ፈጻሚ አካላትን የቴክኒክ አቅም ለመገንባት፣ የአገልግሎት ጥራትና ተደራሽነትን ለማሳደግ እንዲሁም የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ለማጠናከር በርካታ ስትራቴጂያዊ ተግባራትን አከናውኗል።
- በዚህም መሠረት አግባብነት ባላቸው የተለያዩ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ለ670 ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ፣ ከዕቅድ በላይ ለ 571 ተሳታፊዎች (85.2%) የግንዛቤ ማሳደጊያና የቴክኒክ ሥልጠናዎችን መስጠት ተችሏል። በተጨማሪም፣ ምግብ-ወለድ በሽታዎችን ለመከላከል፣ ለመለየትና አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ሰፊ የሥልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት (Training Needs Assessment) በ12 ክልሎች እና በ2 ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በሚገኙ ግንባር ቀደም የጤና ቁጥጥር ባለሙያዎች ላይ የተካሄደ ሲሆን፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር በተደረጉ 4 ዋና ዋና የምክክርና የቫሊዴሽን መድረኮች ላይ በአጠቃላይ 142 ተሳታፊዎች (120 ወንድ እና 22 ሴት) ተሳትፈውባቸዋል። ይህ አፈጻጸም የማዕከሉን የባለሙያዎች የቴክኒክ ብቃት ካፒታል ከማሳደጉም በላይ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የሥራ ትስስር ይበልጥ ያጠናከረ ተግባር ሆኖ ተመዝግቧል።

ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል።

- የላቦራቶሪ የውስጥ ባለሙያዎች ሥልጠና (Training of Lab Staff)
- ይህ የሥልጠና ምድብ የማዕከሉን የውስጥ ሠራተኞች እና የቴክኒክ ባለሙያዎች የምርመራ ብቃት፣ የላቦራቶሪ ጥራት አስተዳደር ሥርዓት እና የሥራ ላይ ደህንነትን ለማሳደግ የተሰጡ ሥልጠናዎችን ያጠቃልላል፦
- የጥራት ሥርዓት እና አክሬዲቴሽን ሥልጠናዎች፦ በኔዘርላንድ ልማት ድርጅት (SNV) ድጋፍ በጥራት ሥርዓት አስተዳደር (ISO/IEC 17025:2017 እና ISO 9001:2015) ላይ ለ58 የማዕከሉ እና የባለስልጣን መ/ቤቱ የእንስሳት ሬጉላቶሪ ዘርፍ የቴክኒክ ባለሙያዎች [40 ወንድ እና 18 ሴት] ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ አክሬዲቴሽን አገልግሎት (EAS) ድጋፍ ደግሞ 2 ከፍተኛ ባለሙያዎች [2 ወንድ] በአክሬዲቴሽን ብቃት ምዘና ላይ ጥልቅ ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል።
- የላቦራቶሪ መሣሪያዎች እና ቴክኒክ አቅም ግንባታ፦ በተባበሩት መንግሥታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት (UNIDO) ድጋፍ በመሣሪያዎች አጠቃቀምና የኮምፕሊያንስ ቬሪፊኬሽን ላይ የ10 ቀን ሥልጠና ለ4 ባለሙያዎች [4 ወንድ] የተሰጠ

ሲሆን፤ በግብርና ሚኒስቴር የዲራይቪ ፕሮጀክት ድጋፍ ደግሞ በዕውቅና ማስቀጠልና ማጽናት፣ በመድኃኒት ጥራትና በምግብ-ወለድ በሽታዎች ሞለኪውላር ምርመራ ሥነ-ዘዴ ላይ ለ36 ባለሙያዎች [28 ወንድ እና 8 ሴት] የንድፈ-ሐሳብ ሥልጠና ተሰጥቷል።

- የውጭ አገር የላቀ ቴክኒክ ሥልጠናዎች፦ በዓለም ምግብና እርሻ ድርጅት (FAO) ድጋፍ 1 ባለሙያ [1 ወንድ] በፀረ-ተህዋሲያን መድኃኒት መላመድ (AMR) ዳሰሳ ጥናትና ናሙና አሰባሰብ ላይ፣ እንዲሁም በዓለም አቀፍ የኢንሴክት ሥነ-ሕይወትና ኢኮሎጂ ጥናት ማዕከል (ICIPE) ድጋፍ 2 ባለሙያዎች [1 ወንድ እና 1 ሴት] በኬንያ ናይሮቢ በማር ጥራትና ደህንነት ምርመራ ዘዴ ላይ የውጭ አገር ሥልጠና አግኝተዋል።
- የተቋማዊ አዋጅ እና የሥራ ላይ ደህንነት ሥልጠናዎች፦ አዲሱን የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1353/2017 መሠረት በማድረግ ለማዕከሉ ጠቅላላ ሠራተኞች ለ65 ተሳታፊዎች [41 ወንድ እና 24 ሴት] የግንዛቤ ማስጨበጫ የተሰጠ ሲሆን፤ በሥራ ላይ ደህንነት እና ጤና አጠባበቅ (Occupational Safety & Health) ዙሪያ ደግሞ ለ90 የማዕከሉ ሠራተኞች [46 ወንድ እና 44 ሴት] የማነቃቂያ ሥልጠና ተሰጥቷል።
- የሰነድ ክለሳ እና የባለሙያዎች ቴክኒክ ሥልጠና፦ በFSRP ፕሮጀክት ድጋፍ አዲስ በተዘጋጁ የጥራት ማኔጅመንት ሰነዶች ዙሪያ ለ46 ባለሙያዎችና አመራሮች [37 ወንድ እና 9 ሴት] ሥልጠና ተሰቷል።
- የባለድርሻ አካላት ሥልጠና እና የምክክር መድረኮች (Training of Stakeholders)
- ይህ ምድብ በተለያዩ ቦታ እና የሥራ ክፍል ውስጥ ተመድበው በመሥራት ላይ ለሚገኙ የባለሥልጣን መ/ቤቱ ባለሙያዎች፣ ከፌደራልና ከክልል ተባባሪ ተቋማት ለተውጣጡ ባለሙያዎች፣አመራሮችና ባለድርሻ አካላት የጋራ ቁጥጥርን እና የአንድ ጤና መርህን ለማጠናከር የተከናወኑ ተግባራትን ያጠቃልላል፦
- የሥነ-ሕይወታዊ ደህንነት እና የቁጥጥር ሥርዓቶች ሥልጠና፦ በግብርና ሚኒስቴር የ-DRIVE ፕሮጀክት ድጋፍ በሁለቱም የሬጉላቶሪ ዘርፍ ለሚገኙ የላቦራቶሪ፣ የኬላዎችና የኢንስፔክሽን ባለሙያዎች በሥነ-ሕይወታዊ ደህንነት እና ጥበቃ (Biosafety & Biosecurity) ላይ ለ112 ተሳታፊዎች [72 ወንድ እና 40 ሴት]፣ እንዲሁም በምግብ

ጥራትና ደህንነት ዓለም አቀፋዊ የቁጥጥር ሥርዓቶች ዙሪያ ለ80 ባለሙያዎችና አመራሮች [47 ወንድ እና 33 ሴት] ሥልጠና ተሰጥቷል።

- የክልል እንስሳት ጤና ላቦራቶሪ ባለሙያዎች ቴክኒክ ሥልጠና፦ በUNIDO ድጋፍ ደግሞ ከፌደራልና ከክልሎች ለተውጣጡ 30 ባለሙያዎች [28 ወንድ እና 2 ሴት] በሥጋ ምርት የመድኃኒት ቅሪት ምርመራ ሥነ-ዘዴዎች ላይ ሥልጠና ተሰጥቷል።
- የአንድ ጤና (One Health) እና የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረኮች፦ በአንድ ጤና መርህ ላይ በተመሰረተ የምግብ ወለድ በሽታዎች መከላከል ዙሪያ ለ45 ባለሙያዎች [39 ወንድ እና 6 ሴት] የአሰልጣኞች ሥልጠና (ToT) ተሰጥቷል። በተጨማሪም በFAO የፓንደሚክ ፈንድ ፕሮጀክት ድጋፍ የሥልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ውጤትን ለመገምገም ለ40 ባለድርሻ አካላት [33 ወንድ እና 7 ሴት]፣ ሰባት (7) የሥልጠና ሞጁሎች በማዘጋጀት እና የተዘጋጁ የሥልጠና ሞጁሎች ለማፅደቅ ለ35 የአንድ ጤና አመራር አካላት [29 ወንድ እና 6 ሴት] የቫሊዴሽን አውደ ጥናቶች ተካሂደዋል። በUNIDO ድጋፍም በብሔራዊ የሥጋ ምርት ኬሚካል ቅሪት ቁጥጥር ጋይድላይን ላይ ለ22 ባለሙያዎች [19 ወንድ እና 3 ሴት] የግምገማ አውደ ጥናት ተካሂዷል።

## የመረጃ አቅርቦት ሥርዓት እና አጠቃቀምን ማሻሻል

- የዲጂታል መረጃ አቅርቦት ሥርዓትን ለማሻሻልና መረጃዎችን ለባለሙያዎችና ለአመራሮች ፈጣንና ተደራሽ ለማድረግ የጎግል ድራይቭ ሺት (Google Sheets) ቴክኖሎጂን በስፋት ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል። በዚህም የቋሚና አላቂ የላቦራቶሪ ግብዓቶች ቆጠራ እና ማቀናነሻ ገጽ፣ የግብዓት ግዥ ፍላጎት ማሳወቂያ፣ የስፔስፊኬሽን ማዘጋጃና መገምገሚያ ገጽ፣ እንዲሁም የእንስሳት ምርትና ግብዓት ናሙናዎች የጥራትና ደህንነት ምርመራ ሥራዎች ሂደት መከታተያ ዲጂታል ገጾች ተዘጋጅተው ሙሉ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ።
- ማዕከሉ የመረጃ ማኔጅመንት ሥርዓቱን ሙሉ በሙሉ ዲጂታላይዝ ለማድረግ የሚያስችሉ የዝግጅት ሥራዎችን በበጀት ዓመቱ አከናውኗል። በዚህም መሠረት በግብርና ሚኒስቴር የድራይቭ (DRIVE) ፕሮጀክት የበጀት ድጋፍ እና የአይሲቲ (ICT) ዲፓርትመንት ቴክኒካዊ እገዛ፤ ዘመናዊ የላቦራቶሪ ኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት ሥርዓት (LIMS) ዝርጋታን ለማካሄድ የሚያስችል የአማካሪ/ኮንሰልታንት ቅጥር መረጣ እና

የቅድመ-ዝግጅት ሥራ ሂደቶች ተጠናቆ በ2019 በጀት አመት የማዕከሉን አሰራር ሙሉ በሙሉ ዲጂታላይዝ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል።

## የላቦራቶሪ ግብዓት አቅርቦት ማሳደግ

- በበጀት ዓመቱ ለማዕከሉ ሥራ የሚውሉ ቋሚና አላቂ የላቦራቶሪ ግብዓቶች ፍላጎት ተለይቶ ስፔስፊኬሽኖች የተዘጋጁ ሲሆን፣ የግዥ ሂደቶችም በተሳካ ሁኔታ ተከናውነዋል። በዚህም መሠረት በመንግሥት የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓት (e-GP) አማካኝነት 3,698,676.00 ብር አላቂ ግብዓቶች ግዥ ተከሄዷል። በተጨማሪም በግብርና ሚኒስቴር ዲራይቪ ፕሮጀክት ድጋፍ በአለም አቀፍ ጨረታ አሸናፊ ከሆኑ ሁለት ድርጅቶች ከ2 መቶ ሚሊዩን ብር በላይ የተገዙ ቋሚና አላቂ የላቦራቶሪ ግብዓቶች በተጠየቀው ቴክኒካዊ መግለጫ መሠረት መሆናቸው ተረጋግጦ ገቢ ሆነው ለሥራ እንዲውሉ ተደርጓል።
- የላቦራቶሪ ግብዓት አቅርቦትን ይበልጥ ለማሻሻል ከልማት አጋሮች ጋር ጠንካራ የሥራ ትስስር ተፈጥሯል። በዚህም መሠረት ለኢትዮ-ፓንደሚክ ፈንድ ፕሮጀክት አስተባባሪ ለሆነው የዓለም ጤና ድርጅት (WHO) 177 ልዩ ልዩ ግብዓቶች፣ እንዲሁም ለዓለም ምግብና እርሻ ድርጅት (FAO) 125 የተለያዩ የላቦራቶሪ ግብዓቶች ዝርዝር የግዥ መግለጫ (Specification) ተዘጋጅቶ ተላልፏል። ግዥዎቹ በእነዚሁ የልማት አጋር ድርጅቶች በኩል ተፈጽመው ለማዕከሉ እንዲቀርቡ የቅርብ ክትትል እየተደረገ ይገኛል።
- በዓለም ጤና ድርጅት (WHO) የኢትዮ-ፓንደሚክ ፈንድ ፕሮጀክት ድጋፍ በድምሩ 69,557.07 የአሜሪካ ዶላር ($) ግዥ ተፈጽሞ ለማዕከሉ ገቢ ተደርጓል። ገቢ የተደረጉት ዕቃዎች 25 ዘመናዊ ላፕቶፖች እና 10 ዴስክቶፕ ኮምፒውተሮች ከነሙሉ መለዋወጫዎቻቸው (Accessories) እንዲሁም 3 ቋሚ እና 5 አላቂ የላቦራቶሪ መሣሪያዎችና ግብዓቶች ሲሆኑ፣ በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ ለአገልግሎት ዝግጁ ሆነው ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል።
- ከUNIDO ጋር በተደረገ ትብብር የላቦራቶሪውን የምርመራ አቅም የሚያሳድጉ በርካታ ስኬታማ ተግባራት ተከናውነዋል። በዚህም መሠረት በድምሩ 129,874.33 የአሜሪካ ዶላር ($) የ5 ዘመናዊ የኬሚካል ቅሪት መመርመሪያ መሣሪያዎች የቅድመ-ብልሽት መከላከል፣ የሶፍትዌር ማሻሻያ እና የጥገና አገልግሎት ግዥ የተፈጸመ ሲሆን፤ ለመሣሪያዎቹ የሚሆኑ መለዋወጫዎችና የምርመራ ግብዓቶችም ተሟልተዋል።

ከቴክኒክ ብቃት ግንባታ ጎን ለጎን፣ የብሔራዊ የሥጋ ኬሚካል ቅሪት ቅኝት ጋይድላይን የተዘጋጀ ሲሆን፣ የምርመራ ሥነ-ዘዴ ትክክለኛነት ማረጋገጫ (Validation & Standardization) ሥራዎችም በተሳካ ሁኔታ ተከናውነዋል።

- የማዕከሉ አጠቃላይ ዕድሳት እና የጨረታ ሂደት አፈጻጸም:- የእንስሳት ጥራት ምርመራ ማዕከል ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ምንም ዓይነት ጥገና ያልተደረገለት በመሆኑ በሥራ አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ማነቆ ፈጥሮ ቆይቷል። ይህንን ችግር ከመሠረቱ ለመቅረፍ ከማዕከሉ፣ ከግብርና ሚኒስቴር እና ከብሔራዊ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የተውጣጡ መሐንዲሶችና የቴክኒክ ባለሙያዎች ቡድን ተቋቁሞ የችግሮቹ ዓይነትና መጠን እንዲለዩ ተደርገዋል። ቡድኑ የዕድሳትና ጥገና የዋጋ ግምት (Bill of Quantity - BOQ) እና የጨረታ ሰነዶችን በስማርት መንገድ አደራጅቶ ያጠናቀቀ ሲሆን፤ በግብርና ሚኒስቴር የተቀናጀ የምግብ ሥርዓት ማጠናከሪያ ፕሮጀክት (FSMP) የበጀት ድጋፍ የሚከናወነው ይኸው አጠቃላይ የዕድሳትና ጥገና አገልግሎት ግዥ በአሁኑ ወቅት በግልጽ ጨረታ ሂደት ላይ ይገኛል። ይህ ዕድሳት ሲጠናቀቅ ለሠራተኞች ምቹ የሥራ ከባቢ ከመፍጠሩም በላይ ላቦራቶሪው ዓለም አቀፍ ስታንዳርዱን የጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጥ ያስችላል።

## የመረጃ አቅርቦት ሥርዓት እና አጠቃቀምን ማሻሻል

- በላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ሥርዓት መሠረት የማዕከሉ ዋና ዋና ቴክኒካል መረጃዎች በኤሌክትሮኒክስ ዳታ እና በሰነድ ተደራጅተው ለአገልግሎት እንዲውሉ ተደርጓል። በዚህም መሠረት የናሙና ቅበላ፣ የምርመራ ሰርተፊኬቶች፣ የፕሮፊሼንሲ ፍተሻ ውጤቶች፣ የቁሳቁስና መሣሪያዎች የካሊብሬሽንና ጥገና መረጃዎች፣ ልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ፋርማኮፒያዎች (Pharmacopeias) እና ጋይድላይኖች ተደራጅተዋል። በተጨማሪም የጥራት ማኔጅመንት ሰነዶች (የአሰራር መመሪያዎች፣ የስጋት ትንተናዎች፣ የውስጥና ውጭ ኦዲት ግኝቶች) እና የባለሙያዎች የትምህርት፣ የሥልጠናና የሥራ መዘርዝር መረጃዎች ስትራቴጂያዊ መንገድ ተዋቅረዋል።

## 4. ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች

### የሴቶችን አቅም በመገንባትና እኩል ተጠቃሚነታቸውን በማሳድግ ለቁጥጥር ተግባሩ ያላቸውን ሚና ማጐለበት

- የሥርዓተ-ፆታ ማካተት፣ ጾታዊ ትንኮሳ እና የሰብአዊ መብት ጥሰት  በ በጥቅሉ  20 የስራ ክፍሎች እና ቅርንጫፍ  ጋር በመከናወኑ   አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡
